ቍጥር ፷፰ ፲፱፻፴፮ ዓ ም

የንጉሠ ነገሥቱ የጦር ሠራዊት ተብሎ ለሚሠየም አንድ የጦር ኃይል ማቋቋሚያና አገዛዝ የወጣ አዋጅ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ፤
እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
ቀጥሎ ያለውን አውጀናል ።

፩) ይህ አዋጅ ያ፲፱፻፴፮ ዓ ም የንጉሠ ነገሥቱ የጦር ሠራዊት ማስተዳደሪያ አዋጅ ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፪) በዚህ አዋጅ በቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጠው ካላስፈለገ በተቀር ።

«አዛዥ» ማለት ያንድ ባታዮንና በባታዮኑ ውስጥ የሚገኘው የማናቸውም መኰንንና ወታደር አዛዥ ነው ።

«ጠላት» ማለት የጦር መሣሪያ የያዙ ሴረኞችና ሸፍቶች ሽብር አንሺዎችም ጭምር ነው ።

«እሥራት» ማለት እሥራት የሚቆርጠው ፍርድ ቤት በሌላ አኳኋን ካላሻሻለ በተቀር ከጠንካራ ሥራ ጋር የሚወሰን ነው ።

«የጦር መኰንን» ማለት ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሥልጣን የተሰጠው የጦር ሹም ነው ።

«ወታደር» ሲባል መኰንን አይቀላቅልም ። ነገር ግን በሌላው አኳኋን በዚህ አዋጅ ውስጥ የሚተዳደሩት ሰዎች ሁሉ ማለት ነው ።

«ማናቸውም ሰው» ማለት በወታደርነት ሕግ የሚያድር መኰንን ፤ ወይም ወታደር ማለት ነው ። በዚህ አዋጅ የተጻፈው ማናቸውም አንቀጽ በተለይ ወታደር ላልሆኑ ሰዎች ተዘርዝሮ ካልተጻፈ ወታደር ያልሆነውን ሰው አይነካም ።

ክፍል ፩ ።

ስለሕግና ተግባር ።

፫) (፩) ከጊዜ ጊዜ ለመወሰን እንደሚቻል በንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛታችን ውስጥ አንድ ወይም ከአንድ የሚበልጥ የእግረኛ ባታዮኖችና ሌላም ይህን የመሳሰሉ ወታደሮች እንዲቋቋምና እንዲጠበቅ ይደረጋል ።

No. 68 of 1944.

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT AND GOVERNMENT OF A FORCE STYLED THE IMPERIAL ARMY

CONQUERING LION OF THE TRIBE OF JUDAH
HAILE SELASSIE I
ELECT OF GOD, EMPEROR OF ETHIOPIA

WE PROCLAIM AS FOLLOWS:—

1. This Proclamation may be cited as the Imperial Army Proclamation, 1944.

2. In this Proclamation, unless the context otherwise requires—

« Commanding Officer » means the officer in command of a battalion, and in relation to any officer or soldier means the officer in command of the battalion to which such officer or soldier belongs;

« Enemy » includes all armed mutineers, armed rebels and armed rioters;

«Imprisonment» means imprisonment with hard labour unless the court impossing such imprisonment otherwise orders;

« Officer » means an officer commissioned by His Imperial Majesty or an officer seconded from the British Army;

« Soldier » does not include an officer but otherwise includes every person subject to this Proclamation.

« Person » means an officer or soldier subject to military law, and nothing in this Proclamation shall affect a civilian unless the contrary is specifically stated.

Part I. — CONSTITUTION AND DUTIES

3. (i) There shall be established and maintained in Our Empire one or more battalions of infantry and such other troops as may from time to time be desided.

Scanned by CamScanner

(፪) የጦር ሠራዊቱ የንጉሠ ነገሥት ግዛታችንን ለመከላከልና የመልካም ሥርዓት ጥበቃ አላፊነት የተጣለበት ይሆናል ።

ክፍል) ፪ ።

ስለ ሥርዓት ።

ስለወንጀሎችና ስለቅጣቶች ፤

ስለጦር አገልግሎት ወንጀሎች ።

፬) ማንኛውም ሰው ከዚህ ቀጥሎ ከተመለከቱት አንዳች ጥፋቶች የሚያጠፋ ይህንንም ማለት ።

(፩) በሚያሳፍር አኳኋን የጦር ሠፈር ሥፍራ ቦታ ወይም ጥበቃ ለሚለቅና አሳልፎ የሚሰጥ ሰው ፤ ወይም አገረ ገዥና አዛዥ መኰንን ፤ ወይም ሌሎች ሰዎችም ቢሆኑ ሊከላከሉለት የሚገባቸውን የጦር ሰፈር ሥፍራ ቦታ ፤ ወይም ጥበቃ በሚያሳፍር ሁኔታ እንዲለቁ ፤ ወይም አሳልፈው እንዲሰጡ ለማስገደድ ወይም ለማነቃቃት አንዳች ሥራ የሠራ ፤

(፪) በጠላት ፊት በሚያሳፍር አኳኋን የጦር መሣሪያዎችንና ወይም ዕቃዎችን የሚጥል ፤

(፫) በከሐዲነት ከጠላት ጋር የሚላላክና ለጠላትም ምሥጢር የሚያቀብል ፤ ወይም በፍርሃት ምክንያት ፤ ወይም በእምነት ጉድለት የተነሣ ጦርነቱ እንዲቆም የሰላም ባንዴራ የሚልክ ፤

(፬) ጠላትን በመሣሪያና በጥይት በስንቅም የረዳ ወይም እያወቀ እሥረኛ ያልሆነ ጠላት ያስጠጋ የከለለ ፤

(፭) የጦር ምርኮኛ ሆኖ ሳለ በፈቃዱ ጠላትን ያገለገለ ፤ ወይም የረዳ ፤

(፮) የጦር ሠራዊታችን ፤ ወይም የዚሁ ጦር ክፍል የሆነ የጦርነት ሥራ በሚሠሩበት ሰዓት እያወቀ ሥራቸው እንዳይከናወን ከማድረግ የሚቆጠር አንዳች ሥራ የሠራ ፤

(፯) በጦርነት ጊዜና ወይም በሠፈር የወገንና የጠላት መለያ አጭር ምሥጢራዊ ማስታወቂያ ቃል ፤ ወይም ምልክት በከሐዲነት ፤ ወይም በችላ ባይነት ላንዳች ሊያውቀው ለማይገባው ሰው የሚገልጽ ፤ ወይም ከተነገረው ሌላ ልዩ የሆነ ምሥጢራዊ የመታወቂያ ቃል ፤ ወይም ምልክት የሚሰጥ ፤

በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ የሞት ፍርድ ይፈረድበታል ።

፭) ማንኛውም ሰው በጦር ሜዳ ላይ ሳለ ፤

(፩) ከበላይ ሹሙ ሳይታዘዝ እሥረኞች ፤ ወይም ፈረሰኞች ለመጠበቅ ፤ ወይም ቁስለኞች ወደኋላ ለመውሰድ በሐሰት በማስመሰል የተሰለፈበትን ቦታ ለቆ የሔደ ፤

(፪) ያለአለቃው ትእዛዝ በፈቃዱ ማንኛቸውንም ዕቃዎች ያጠፋ ፤ ወይም የጐዳ ፤

(፫) እንደሚገባ ባለመጠንቀቅ ፤ ወይም የተሰጡትን ትእዛዛት ባለመጠበቅ ፤ ወይም በገዛ ፈቃዱ ሥራ ቸለል በማለት በምርኮኛነት የተያዘ ወይም ከተማረከም በኋላ እንደገና ወደጦር ሠራዊታችን ለመቀላቀል ችሎት እያለው ሳይቀላቀል የቀረ ፤

(፬) የሚገባ ሥልጣን ሳይኖረው ከጠላት ጋር የሚላላክና ምሥጢር የሚገልጽ ፤ ወይም የጦርነት ማቆሚያ ነጭ ባንዴራ የሚልክ ፤

(፭) በቃል ወይም በጽሕፈት ፤ ወይም በምልክቶች ወይም በሌላ አኳኋን አስፈላጊ ያልሆነ የሚያሸብር ጩኸትና ተስፋ የሚያስቆርጥ ወሬ የሚነዛ ፤

(፮) ጦርነት በሚደረግበትም ሰዓት ሆነ ፤ ወይም ወደ ጦርነት ከመሔድ አስቀድሞ የማሸበርና ተስፋ የማስቆረጥ ስሜት ያላቸው ቃላት የሚናገር ፤

(ii) The army shall be charged with the defence of Our Empire and the maintenance of good order.

Part II. — DISCIPLINE

CRIMES AND PUNISHMENTS.

Offences in respect of Military Service.

4. Any person who commits any of the following offences, that is to say:—

(i) shamefully abandons or delivers up any garrison, place, post or guard, or uses any means to compel or induce any Governor, commanding officer or other person shamefully to abandon or deliver up any garrison, place, post or guard which it was the duty of such Governor, officer or person to defend;

(ii) shamefully casts away his arms, ammunition or tools in the presence of the enemy;

(iii) treacherously holds correspondence with or gives intelligence to the enemy, or treacherously or through cowardice sends a flag of truce to the enemy;

(iv) assists the enemy with arms, ammunition or supplies, or knowingly harbours or protects an enemy not being a prisoner;

(v) having been made a prisoner of war, voluntarily serves with or voluntarily aids the enemy;

(vi) knowingly does when on active service any act calculated to imperil the success of Our forces or any part thereof;

(vii) while on active service treacherously makes known the parole, watchword or countersign to any one not entitle to receive it, or treacherously gives a parole, watchword or countersign different from that which he received;

is guilty of an offence and shall be sentenced to death.

5. Any person who on active service:—

(i) without orders from his superior officer leaves the ranks in order to secure prisoners or horses, or on pretence of taking wounded men to the rear;

(ii) without orders from his superior officer wilfully destroys or damages any property;

(iii) is taken prisoner, by want of due precaution, or through disobedience of orders, or wilful neglect of duty, or having been taken prisoner fails to rejoin our service when able to rejoin the same;

(iv) without due authority either holds correspondence with, or gives intelligence to, or sends a flag of truce to the enemy;

(v) by word of mouth, or in writing, or by signals or otherwise, spreads reports calculated to create unnecessary alarm or despondency;

(vi) inaction, or previously to going into action, uses words calculated to create alarm or despondency;

Scanned by CamScanner

(፯) በጠላት ፊት ፍርሃትን ለማሳየት ባንዳች ሁኔታ ራሱን ያላገባብ የሚመራ ፤ ወይም ሌሎች አላገባብ እንዲመሩ ያደረገ ፤

በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

፮) (፩) ማናቸውም ሰው ፤

(ሀ) ዘረፋ ለመፈለግ የጦር አዛዡን ጥሎ የሚሔድ ።

(ለ) አንድ ጠባቂ (ጋርድ) የሚገፋ ፤

(ሐ) አንድ ሳንቲኔል የሚቋቋም ፤ ወይም የሚመታ ፤

(መ) ዘረፋ ለመፈለግ ማናቸውንም ቤት ፤ ወይም ሌላ ቦታ ጥሶ በኃይል የሚገባ ፤

(ሠ) ወታደር ሆኖ በሳንትኔልነት ሲሠራ ፀሚቆምበት ቦታ የሚተኛ ወይም የሚሰክር ፤

(ረ) ያለአለቃው ትእዛዝ ጥበቃውን ፤ ምርመራውን ስለላውንና ቦታውን የሚለቅ ፤

(ሰ) በጦርነት ውስጥ በጉዞ ላይ በጦር ሜዳና በማናቸውም ቦታ ሆነ በመተኰስ ጐራዴ በመምዘዝ ፤ ነጋሪት በመምታት ፤ ምልክቶች በማድረግ ፤ በመነጋገር ፤ ወይም በማናቸውም አኳኋን ፤ እያወቀ ወይም በቸልተኛነት የውሸት ሽብሮች የሚያስነሣ ፤

(ቀ) ወታደር ሆኖ በሰንትኔልነት ሲሠራ በደንብ ተቀያሪ ሳይተካለት ጥበቃውን የለቀቀ ፤

በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

(፪) ማናቸውም ሰው ፤

(ሀ) ለኛም ጦር ሠራዊት ሆነ ፤ ወይም ከኛ ጦር ሠራዊት ጋር በጓደኝነት አብረው ለሚሠሩ ጦር ሠራዊት ስንቅና ማናቸውንም አስፈላጊ ነገሮች በሚያመጣ በማናቸውም ሰው ላይ የኃይል ሥራ ያደረገ ፤ ለጦር ሠራዊታችን የሚጠቅመውን ማናቸውንም ነገር የሚቃወም ፤

(ለ) ለራሱ ጦር ክፍል ያልተሰጠውንና ወደ ሌላ ይህን ለመሳሰሉ ጦር ሠራዊቶች የተላኩትን መሣሪያዎችና ስንቆች ከተሰጠው ትእዛዝ በመተላለፍ አላገባብ የያዘ፤ ወይም የከተተ በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

፯) ማመፅና አለመገዛት ፤

ማናቸውም ሰው ።

(፩) በጦር ሠራዊታችን ውስጥ ዐመፅን ፤ ወይም ክሕደትን የሚያስነሣ ፤ ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር ለማንሣት ምክንያት የሚሆንና የሚያብር ፤

(፪) ለኛ ታማኝነቱን ያጸናውን ሰው ታማኝነቱን እንዲያጉድል ለማባበል የሚጣጣር ፤ ወይም ከዚህ በፊት ከተባሉት ጦር ሠራዊቶቻችን አንደኛው ውስጥ ያለውን ማንኛቸውንም ሰው በዐመፅ ውስጥ እንዲተባበር ፤ ወይም እንዲመስጥ ለማድረግ የሚገፋፋ ፤

(፫) በማናቸውም ጦር ሠራዊቶቻችን ውስጥ አንዳች የሴረኝነትንና የዐመፅኝነትን ሥራ ሲያደርግ ያበረ ፤ ወይም እዚያው እያለ ይህን ለማስቀረት እስከ መጨረሻው ሙከራዎቹን ያላደረገ ፤

(፬) እላይ ከተባሉት ጦር ሠራዊቶች ውስጥ አንዳች ያመፀኝነት ፤ የከሐዲነት ሥራ መሠራቱን ፤ ወይም ሊደረግ መታሰቡን እያወቀ ለአዛዥ መኰንኑ ፤ ወይም ለሌላ የዚሁ ክፍል ለሆነ ለበላይ መኰንን ያለመዘግየት ያላስታወቀ በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል። በጦርነት ላይ የሆነ እንደሆነ የሞት ፍርድ ይፈረድበታል ።

፰) ማናቸውም ሰው የበላይ መኰንኑን የመታና የኃይል ነገር ያደረገ የዛተበትና የኃይል ቃል የተናገረ በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

(vii) misbehaves or induces others to misbehave before the enemy in such a manner as to show cowardice;

is guilty of an offence.

6. (1) Any person who:—

(i) leaves his commanding officer, to go in search of plunder;

(ii) forces a safeguard;

(iii) forces of strikes a sentinel;

(iv) breaks into any house or other place in search of plunder;

(v) being a soldier acting as a sentinel, sleeps or is drunk at his post;

(vi) without orders from his superior officer, leaves his guard, picket, patrol or post;

(vii) by discharging firearms, drawing swords, beating drums, making signals, using words, or by any means whatever, intentionally or negligently occasions false alarms in action, on the march, in the field, or elsewhere;

(viii) being a soldier acting as a sentinel leaves his post before he is regularly relieved;

is guilty of an offence.

(2) Any person who:—

(i) does violence to any person bringing provisions or supplies to the forces, whether Our forces or forces co-operating therewith;

(ii) irregularly detains or appropriates to his own unit any provisions or supplies proceeding to any such forces aforesaid, contrary to orders issued in that respect;

is gualty of an offence.

MUTINY AND INSUBORDINATION.

7. Any person who:—

(i) causes or conspires with any other persons to cause any mutiny or sedition in any of Our forces;

(ii) endeavours to seduce any person from allegiance to Us, or to persuade any person in any of Our forces to join in any mutiny or sedition;

(iii) joins in or, being present, does not use his utmost endeavours to suppress, any mutiny or sedition in any of Our forces;

(iv) knowing of any actual or intended mutiny or sedition in any such force as aforesaid does not without delay inform his commanding officer or other superior officer of the same;

is guilty of an offence, and if on active service shall be sentenced to death.

8. Any person who strikes or uses or offers any violence to or uses threatening or insubordinate language to his superior officer, is gualty of an offence.

፱) ማናቸውም ሰው የበላይ መኰንኑ በቃልም ሆነ በጽሕፈት ፤ ወይም በምልክት ፤ ወይም በሌላ አኳኋን ከሕግ የተባበረ ትእዛዝ ሲያዘው የማይታዘዝ በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል።

፲) ማናቸውም ሰው ፤

(፩) አምባጓሮ ድብድብ ብጥብጥ አድርጎ ሳለ ማናቸውም መኰንን (በማዕርግ ምንም ዝቅተኛ ቢሆን እንኳን) እንዲያዝ ትእዛዝ ሲሰጠው አልታዘዝም ብሎ የጦር መኰንን የሚመታ ወይም የድፍረት ነገር የሠራ ፤

(፪) ታሥሮ ሲጠበቅ ሳለ ማናቸውንም ሰው በጦር ሕግ ውስጥ ቢሆንም ባይሆንም የሚጠብቀውን ሰው የሚመታ ወይም የድፍረት ሥራ የሠራ ፤

(፫) በኀላፊነት እንዲይዘውና እንዲጠብቀውም ሥራው የሚሆነውን ሰው የሚቋቋም (የሚቃወም) ፤

(፬) ከጦር ወታደር ቤቶች ከሰፈር ወይም ከጦር ጣቢያ ዎች ሠብሮ ወይም ጥሶ የወጣ ማናቸው ም ሰው በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

፲፩) ለማናቸውም ጠቅላላ ትእዛዝና በወታደር ሰፈር የሚሰጠውንና ሌሎችንም ትእዛዞች ለመታዘዝ ቸላ ያለ በጥፋቱ በደለኛ ሁኖ ይቀጣል ።

ስለከዳትና ያለፈቃድ ከሥራ መታጣት ።

፲፪) ማናቸውም ሰው ፤

(ሀ) ከኛ አገልግሎት የሚከዳ ወይም ለመከዳት የሚሞክር ።

(ለ) በዚህ አዋጅ ውስጥ የሆነውን ማናቸውንም ሰው ከኛ አገልግሎት እንዲከዳ የሚያደርግ ፤ ወይም ለማድረግ የሚጣጣር ፤ ወይም ለራሱ ሥራ የሚያስኮበልልና ለማስኮብለልም የሚጣጣር በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

፲፫) ማናቸውም ሰው ፤

(፩) ማናቸውንም ሰው ካገልግሎታችን ሲኮበልል ያገዘ፤

(፪) በዚህ አዋጅ ውስጥ የሆነውን የማናቸውንም ሰው መከዳት ወይም ለመከዳት ማሰቡን እያወቀ ለአዛዥ መኰንኑ ያላስታወቀ ወይም ኮብላዩን ፤ ወይም ለመኮብለል ያቀደውን በራሱ ችሎት እንዲያዝ አንዳች ነገር ያላደረገ በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

፲፬) ማናቸውም ሰው ፤

(፩) ከሥራው ያለፈቃድ የሚታጣ ።

(፪) በሰልፍ ሜዳ ወይም አዛዥ መኰንኑ ባመለከተው የቀጠሮ ቦታ ከመገኘት የሚተጓጐል ፤ ወይም ከዚያ ፈቃድ ሳይሰጠውና ሳይቀየርለት የሚሔድ ፤ ወይም አስገዳጅ ጉዳይ ሳያገኘው ከሰልፍ ውስጥ ሾልኮ የሚሔድ ፤

(፫) በሠፈር ወይም በጦር ምሽግ ፤ ወይም በሌላ ዘንድ ሆኖ ሳለ ከተወሰኑት ድንበሮች ፤ ወይም በጠቅላላና በጦር ሠፈር ፤ ወይም በሌላ ትእዛዝ ከተከለከለው ከማናቸውም ወሰን የይለፍ ወይም የፈቃድ ወረቀት ከአዛዥ መኰንኑ ሳይኖረው አልፎ በተከለከለው ቦታ የሚገኝ ።

(፬) በዚያ እንዲገኝ በሚገባ ከታዘዘበት ከማናቸውም ተማሪ ቤት ከአዛዥ መኰንኑ ፈቃድ ሳይኖረው ፤ ወይም የሚበቃ ምክንያት ሳይኖረው የታጣ በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

የሚያሳፍር ምግባር ።

፲፭) ማናቸውም ሰው የሰው ገንዘብ የሚቀማ ወይም በቅሚያ ውስጥ የሚያብር በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

፲፮) (፩) ማናቸውም ሰው እንዲጠብቅ ፤ ወይም እንዲያካፍል አላፊነት የተጣለበትን የሕዝብ ፤ ወይም የጦር ሠራዊት ገንዘብ ፤ ወይም ዕቃዎች የሚሰርቅ በተንኰል ያለአገባብ ሥራ

9. Any person who disobeys any lawful command given by his superior officer, whether the same is given orally, in writing or by signal, or otherwise, is guilty of an offence.

10. Any person who:—

(i) being concerned in any quarrel, fray or disorder, refuses to obey any officer (though of inferior rank) who orders him into arrest, or strikes or uses or offers violence to any such officer;

(ii) strikes, or uses or offers violence to any person, whether subject to military law or not, in whose custody he is placed;

(iii) resists an escort whose duty it is to apprehend him or to have him in charge;

(iv) breaks out of barracks, camp, or quarters, is guilty of an offence.

11. Any person who neglects to obey any general, garrison or other orders is guilty of an offence.

DESERTION AND ABSENCE WITHOUT LEAVE

12. Any person who:—

(a) deserts or attempts to desert Our service;

(b) persuades or endeavours to persuade, procures or attempts to procure, any person subject to this Proclamation to desert Our service;

is guilty of an offence.

13. Any person who:—

(a) assists any person subject to this Proclamation to desert from Our service;

(b) being cognisant of any desertion or intended desertion of a person subject to this Proclamation, does not forthwith give notice to his commanding officer, or take any steps in his power to cause the deserter or intended deserter, to be apprehended;

is guilty of an offence.

14. Any person who:—

(a) absents himself without leave;

(b) fails to appear at the place of parade or rendezvous appointed by his commanding officer, or goes from thence without leave before he is relieved, or without urgent necessity quits the ranks;

(c) when in camp, or garrison, or elsewhere, is found beyond the limits fixed or in any place prohibited by any general, garrison or other order without a pass or written leave from his commanding officer;

(d) without leave from his commanding officer, or without due cause, absents himself from any school when duly ordered to attend there;

is guilty of an offence.

DESGRACEFUL CONDUCT.

15. Any person who commits or connives at any extortion is guilty of an offence.

16. (a) Any person who being charged with or concerned in the care and distribution of any public or army money or goods, steals, fraudulently misap-

የሚያሲዝ ወይም በማይገባ ለራሱ የሚወስድ ፤ ወይም በስርቆሹ ፤ በተንኮል ሥራ በማስያዝ ፤ ወይም ለራሱ በመውሰድ አብሮ የሚገኝ፤ወይም ከዚያው ላይ በራሱ ፈቃድ ዕቃዎችን የሚያበላሽ በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

(፪) የባልንጀራውን ወይም ያንድ መኰንን ገንዘብና ዕቃዎች እንዲሁም የጦር ሠራዊት ክበብ ተቀማጭ ገንዘብ ፤ ወይም ዕቃዎች ፤ ወይም ለጦር ሠራዊት የተመደበ ፤ ወይም የመንግሥት የሆነ ገንዘብ ፤ ወይም ዕቃዎች የሰረቀና አታሎ የወሰደ ፤ ወይም የስርቆሽና አለአገባብ የተወሰደ መሆኑን እያወቀ የሚቀበል በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

፲፯) ማናቸውም ሰው ፤

(፩) ሥራ እንዳይሠራ ታመምኩ ብሎ የሚለግም ሐሰት ምክንያት የሚያበጅ ወይም ሕመምና ደካማነትን በውሸት የሚያበቅል ፤

(፪) በፈቃዱ ራሱን ፤ ወይም ሌላውን ወታደር ለጦር ሥራ እንደማይስማማ ያደረገ ፤ ወይም ያቈሰለ በቈሳዩ ወታደር ልመናም ቢሆን ባይሆንም ለጦር ሥራ ራሱን ወይም ወታደሩን እንዳይስማማ ለማድረግ አስቦ ያቈሰለ እንዲሁም ራሱ ለጦር አገልግሎት የማይስማማ እንዲሆን ባንዳች በሌላ ሰው ሰውነቱን ያስቈሰለ ወይም ጉዳት ያስደረገ ።

(፫) በሆስፒታልም ሆነ በሌላ ዘንድ አለአገባብ በክፉ ጠባይ ፤ ወይም ባለመታዘዝ ሕመምን ፤ ወይም ጉድለትን በማባባስ ምኞት ወይም ከመዳን ለመዘግየት ፍላጎት ላንዳች ትእዛዞች በፈቃዱ በክፉ ጠባይ ፤ ወይም ትእዛዝን ባለመከተል ጥፋተኛ የሚሆን በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

ስ ካ ር ።

፲፰) ማናቸውም ሰው በሥራ ላይ ሳለ ፤ ወይም ሥራ ፈቶም ቢሆን ሰክሮ ቢገኝ በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

በእሥረኞች ምክንያት የሚፈጸም ጥፋት ።

፲፱) ማናቸውም ሰው ።

(፩) ያንድ ጥበቃ ፤ ምርመራ ፤ ስለላ ፤ ወይም ቦታ አዛዥ ሆኖ ሳለ የሚገባ ፈቃድ ሳያገኝ በፈቃዱም ሆነ በሌላ አኳኋን ማናቸውም በእርሱ አላፊነት እንዲጠበቅ የተሰጠውን ሰው የሚለቅ ፤

(፪) በዘበኝነት እንዲጠብቀው በእርሱ አላፊነት የተሰጠውን ሰው በፈቃዱ ወይም የሚበቃ ምክንያት ሳይኖረው እንዲያመልጥ ያደረገ በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

፳) ማናቸውም ሰው አንድ የተያዘን ፤ ወይም የታሠረን ሰው ለምርመራ በባለሥልጣኖች ፊት ሳያቀርብ ያዘገየ ወይም እንዲመረመር ከደንበኛ ባለሥልጣን ፊት ነገሩን ሳያቀርብ የቀረ፤ ወይም በሌላ አኳኋን አለአገባብ ሰው ይዞ የሚያቆይ በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

፳፩) ማናቸውም ሰው ተይዞ ወይም ታሥሮ ሳለ ከእሥር ቤት ወይም ከሌላ በደንበኛ ከሆነ ጥበቃ ውስጥ የኰበለለ ፤ ወይም ለመኰብለል የሞከረ በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል።

በንብረት የተነሣ ስለሚፈጸሙ ጥፋቶች ።

፳፪) ማናቸውም ሰው ፤

(፩) የሚገባ ሥልጣን ሳይኖረው ካንዳች ሰው ላይ ከጋሪ ፤ ወይም ከተሸከርካሪ ፤ ከጭነት ፤ ወይም ከተሸካሚ ይህን ከመሰለው ሁሉ በኃይል ገንዘብ የሚወስድ ፤

(፪) ለማንኛውም የጦር ሠፈርና ምሽግ ፤ ወይም ጣቢያ ቦታና ቤት የመጣውን ዕቃና ሸቀጥ በዚያ አንዳች የማዘዝ ወይም የሥልጣን ችሎታ ያለው ሰው በዕቃው ላይ ቀረጥ በማድረግ ለራሱ ገቢ ገንዘብ ቢያደርግ፤ ወይም በመግዛትና

plies, or embezzles the same, or is concerned in or connives at the stealing, fraudulent missapplication or embezzlement thereof, or wilfully damages any such goods, is guilty of an offence.

(b) steals, or embezzles, or receives knowing them to have been stolen or embezzled, any money or goods the property of a comrade or of an officer, or any money or goods belonging to any army mess or band, or to any army institution or any public money or goods;

is guilty of an offence.

17. Any person who:—

(a) malingers, or feigns or produces infirmity or disease;

(b) wilfully maims or injures himself or any other soldier, whether at the instance of such soldier or not, with intent thereby to render himself or such other soldier unfit for service, or causes himself to be maimed or injured by any person with intent thereby to render himself unfit for service;

(c) is wilfully guilty of any misconduct or wilfully disobeys, whether in hospital or otherwise, any orders, by means of which misconduct or disobedience he produces or aggravates disease or infirmity or delays cure;

is guilty of an offence.

DRUNKENNESS.

18. Any person who commits the offence of drunkenness, whether on duty or not on duty, is guilty of an offence.

OFFENCES IN RELATION TO PRISONERS.

19. Any person who:—

(a) when in command of a guard, picket, patrol or post releases without proper authority, whether wilfully or otherwise, any person committed to his charge;

(b) wilfully or without reasonable cause allows to escape any person who is committed to his charge, or whom it is his duty to keep or guard;

is guilty of an offence.

20. Any person who unnecessarily detains a person in arrest or confinement without bringing him to trial or fails to bring his case before the proper authority for investigation or who otherwise unlawfully detains any person, is guilty of an offence.

21. Any person who, being in arrest or confinement, or in prison or otherwise in lawful custody, escapes or attempts to escape, is guilty of an offence.

OFFENCES IN RELATION TO PROPERTY.

22. Any person who:—

(a) without proper authority exacts from any person, carriage, porterage or provisions;

(b) lays any duty upon, or takes any fee or advantage in respect of, or is in any way interested in, the sale of provisions or merchandise brought into any garrison, camp, station, barracks or place, in which he has any command or authority, or the

Scanned by CamScanner

በመሸጥ ባንዳች ረገድ ለራሱ ጥቅም የሚፈልግ በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

፳፫) ማናቸውም ሰው ።

(፩) የጦር መሣሪያዎቹንና ጥይት ፤ ኤኬፕማውንና ዕቃ ዎቹን ልብሶቹንና ለጦር ሠራዊት አስፈላጊ የሚሆኑትን ነገሮች ሁሉ ፤ ወይም በእርሱ እጅ የሚገኙትን እንስሳዎች ያሸሸ ፤ ወይም ከሚያሸሽ ጋር ያበረ ።

(፪) በዚህ አንቀጽ ውስጥ በፊት ከተዘረዘሩት አንዳች ነገር በቸልተኛነት የሚጥል ፤

(፫) ከዚህ በፊት በዚሁ አንቀጽ ውስጥ ከተመለከቱት ነገሮች ፤ ወይም ያንድ ባልንጀራን ፤ ወይም ያንድ መኰንን ወይም የጦር ሠራዊት የክለብ ቤት ወይም ለጦር ሠራዊት መቋቋሚያ የተመደበ፤ ወይም ማናቸውንም የሕዝብ ንብረትና ዕቃዎች በፈቃዱ የሚጐዳና የሚያበላሽ በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

በሐሰት ማስረጃዎችና ማስታወቂያዎች ስለሚፈጸሙ ጥፋቶች ።

፳፬) ማናቸውም ሰው ፤

(፩) ባንዳች ራፖር ውስጥ ማስታወቂያ እስታቲስቲክና የስም መጥሪያ መዝገብ የደመወዝ መክፈያ ዝርዝር የምስክር ወረቀት መዝገብ ወይም ሌላ ዐይነት ማስታወቂያዎች ማዘጋጀትና መፈረም ሥራው ሆኖ ሳለ እያወቀ የተሳሳተ በማስመሰል ፤ ወይም በተንኰል መንፈስ አንዳች ጒድለት ቢያደርግ ፤ ወይም ሌላው አዘጋጅቶ ትክክለኛ ለመሆናቸው ማረጋገጥ ሥራው ሆኖ ሳለ በምሥጢር በማበር በሐሰትና በተንኰል ሐሳብ ሲታወቀው ሳያስተካክል የሚቀር ፤

(፪) እንዲጠብቅና ሲፈለግም እንዲያቀርብ በእጁ የተቀመጠውን ማናቸውንም ማስረጃ ወረቀት እያወቀ አንዳች ሰው በመጕዳት ሐሳብ ፤ ወይም እያወቀ በተንኰል ሐሳብ የሚያጠፋ የሚያበላሽ የሚለውጥ ፤ ወይም የሚያሸሽ ።

(፫) ስለ አንዳች ጉዳይ ማስታወቂያ ለማውጣት ከመንግሥት በተሰጠው ሥራ እያወቀ የውሸት ማስታወቂያ የሚያወጣ ።

በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

፳፭) ማናቸውም ሰው ፤

(፩) ገንዘብ ለመክፈል ለጦር መሣሪያዎች ለጥይት ፤ ለኤኬፕማ ለልብስ ፤ ለሬዢማ አስፈላጊ ለሚሆኑ ነገሮች፤ ለስንቅ ለቤት ዕቃ ፤ ለመኝታ ፤ ለብርድ ልብስ ፤ ለአልጋ ልብስ ለማብሰያ ዕቃዎች ፤ ለከብት ቀለብ ፤ ለግምጃ ቤት ዕቃዎች በነዚህ ምክንያት ገንዘብ እንዲከፈልበት የሚያዘጋጅ ማስታወቂያ በመፈረም ጊዜ ፊርማው ምስክር የሚሆንበትን ነገር በያንዳንዱ ክፍል ዕቃ ውስጥ የዕቃውን ዐይነትና ስም ሳይጽፍ ባዶ ቦታ የሚተው ፤

(፪) አንድ ራፖር ፤ ወይም እስታቲስቲክ ማዘጋጀት ፤ ወይም መላክ ሥራው ሆኖ ሳለ ለማዘጋጀትና ለማስገደድ እንቢ ያለ ፤ ወይም በሚያስቀጣ ቸልተኛነት የሚያጓድል፤

በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

፳፮) ማናቸውም ሰው ፤

(፩) ወታደር ሆኖ ውሸት መሆኑ ሲታወቀው በማናቸውም መኰንን ፤ ወይም ወታደር ላይ የሐሰት ክስ የሚያቀርብ ።

(፪) ወታደር ሆኖ ራሱን የተበደለ አስመስሎ ጩኸት ሲያቀርብ ያንድ መኰንን ፤ ወይም ምክትል ሹማምንቶች ምግባር የሚነካ አንዳች የሐሰት ማመልከቻ እያወቀ የሚያቀርብ

sale or purchase of any provisions or stores; is guilty of an offence.

23. Any person who:—

(a) makes away with, or is concerned in making away with his arms, ammunition, equipment, instruments, clothing, army necessaries, or any animal of which he has charge;

(b) loses by neglect anything before in this Article mentioned;

(c) wilfully injures anything in this Article mentioned or any property belonging to a comrade, or to an officer, or to any army mess or band, or to any army institute, or any public property;

is guilty of an offence.

OFFENCE IN RELATION TO FALSE DOCUMENTS AND STATEMENTS.

24. Any person who:—

(a) in any report, return, muster roll, pay list, certificate, book, or other document made or signed by him, or of the contents of which it is his duty to ascertain the accuracy, knowingly makes or is privy to the making of, any false or fraudulent statement, or knowingly makes, or is privy to the making of, any ommission with intend to defraud;

(b) knowingly and with intent to injure any person, or knowingly and with intent to defraud, suppresses, defaces, alters or makes away with any document which it is his duty to preserve or produce;

(c) where it is his official duty to make a declaration respecting any matter, knowingly makes a false declaration;

is guilty of an offence.

25. Any person who:—

(a) when signing any document relating to pay, arms, ammunition, equipment, clothing, regimental necessaries, provisions, furniture, bedding, blankets, sheets, utensils, forage or stores, leaves blank any material part for which his signature is a voucher;

(b) refuses, or by culpable negligence omits, to make or send a report or return which it is his duty to make or send;

is guilty of an offence.

26. Any person who:—

(a) being a soldier, makes a false accusation against any officer or soldier, knowing such accusation to be false;

(b) being a soldier, in making a complaint where he thinks himself wronged, knowingly makes any false statement affecting the character of any

Scanned by CamScanner

ወይም እያወቀ በፈቃዱ እውነት የሆኑትን ነገሮች የሚደብቅ ፤

(፫) ወታደር ሆኖ የስንብት ቀን እንዲረዝምለት ለጦር ፤ ወይም ለሲቪል ሹም በፈቃዱ አንዳች የሐሰት ማመልከቻ የሚያደርግ በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

የጦር ፍርድ ቤቶችን በመድፈር ስለሚፈጸሙ ጥፋቶች ።

፳፯) (፩) ማናቸውም ሰው ፤

(ሀ) እንዲቀርብ በሚገባ ተጠርቶ ሳለ ፤ ወይም ባንድ የጦር ፍርድ ቤት ለምስክርነት እንዲቀርብ ታዞ ሳለ ከመቅረብ የሚተጓጐል ።

(ለ) አንድ የጦር ፍርድ ቤት በሕግ ለፈለገው ነገር ለመማል በሥርዓት ለማስረዳት ፤ ወይም ለማረጋገጥ እንቢ የሚል ፤

(ሐ) የጦር ፍርድ ቤት እንዲቀርብለት በሕግ የሚፈልገውን በእጁ የሚገኘውን ፤ ወይም በሥልጣኑ ውስጥ ያለውን ማንኛቸውንም የማስረጃ ወረቀት ለማቅረብ እንቢ የሚል፤

(መ) ምስክር ሆኖ የጦር ፍርድ ቤት መልስ እንዲሰጥ በሕግ ሲጠይቀው መልስ ለመስጠት እንቢ የሚል ፤

(ሠ) የጦር ፍርድ ቤት ችሎት አድርጎ ሳለ በንቀት የሚሳደብ ፤ የሚዝት ፤ በንግግር መሐል በመግባት የሚያቋርጥ ወይም የሚያስቸግር በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

(፪) የጦር ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ከተመለከተው ጥፋት በደለኛ ሆኖ የሚገኘውን ሰው ባጭሩ ነገሩን በዳኝነት ለማየትና ፍርድ ለመስጠት ይችላል ።

፳፰) ማናቸውም ሰው በጦር ፍርድ ቤት ፤ ወይም በዚህ አዋጅ መሐላ ለማስፈጸም ሥልጣን በተሰጠው የፍርድ ቤት ወይም መኰንን ፊት ቀርቦ እንዲምል በሥርዓትም እንዲያስረዳ ፤ ወይም እንዲያረጋግጥ ሲመረመር በፈቃዱ የሐሰት ቃል የሚያቀርብ በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ። ነገር ግን በ፳፯ኛውና በ፳፰ኛው ክፍል የተጻፉትን አንቀጾች የበደለ በወታደርነት ደንብ ያልገባ ሰው የሆነ እንደሆነ በሲቢል ፍርድ ቤት ቀርቦ ለዚሁ ቅጣት በወንጀለኛ መቅጫ በተጻፈው አንቀጽ ፤ ወይም ወታደር ላልሆኑት ሰዎች በወጣው በነጋሪት ጋዜጣ መሠረት ይቀጣል ።

ስለ ልዩ ልዩ የጦር ጥፋቶች ።

፳፱) ማናቸውም ሰው እኛን የሚነካ የክሕደትና እምነት የሚጐድላቸው ቃላት የሚናገር በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

፴) ማናቸውም ሰው የሚገባ ፈቃድ ሳይኖረው የማናቸውንም ጦር ሠራዊት ቁጥር ፤ ወይም ሁኔታዎች ወይም መጋረጃ ቤቶችና ዕቃ ቤቶች ወይም የጦር ሠራዊት መደርጀትን ፤ ወይም ስለ ጦርነቶችና ስለጦር ሠራዊት ጉዞዎች የሚሰጡትን ትእዛዞች በእኛ ሥራ ላይ ጉዳት በሚያደርስ አኳኋን የሚገልጽ ፤በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

፴፩) ማናቸውም ምክትል ሹም ።

(፩) ማናቸውንም ወታደር የመታ ፤ ወይም በሌላ አኳሆን የበደለ ።

(፪) የጦር መኰንን ፤ ወይም የወታደርን ደመወዝ ተቀብሎ በማይገባ ያቆየ ወይም ያንኑ በሚገባው ጊዜ ለመክፈል ያለሕግ የሚከለክል በጥፋቱ በደለኛ ሆኖ ይቀጣል ።

፴፪) ማናቸውም በዚህ አዋጅ ውስጥ የሆነ ሰው በማናቸውም ሥራ ላይ በምግባር አመራር ፤ በደንብ ባለመገኘት ጥፋተኛ የሚሆን ፤ ወይም ለመልካም ትእዛዝና ለጦር ሥርዓት በተ

officer or soldier, or knowingly or wilfully suppresses any material facts;

(c) being a soldier, makes a wilfully false statement to any military or civil officer in respect of the prolongation of furlough;

is guilty of an offence.

OFFENCES IN RELATION TO COURTS MARTIAL.

27. (1) Any person who:—

(a) being duly summoned or ordered to attend as a witness before a court-martial, makes default in attending;

(b) refuses to take an oath or make a solemn declaration or affirmation legally required by a court-martial to be taken or made;

(c) refuses to produce any document in his power or control legally required by a court-martial to be produced by him;

(d) refuses, when a witness, to answer any question to which a court-martial may legally require an answer;

(e) is guilty of contempt of court by using insulting or threatening language, or by causing any interruption or disturbance in the proceedings of such court;

is guilty of an offence.

(2) A court-martial may deal summarily with any person guilty of an offence under this Article.

28. Any person who, when examined on oath or solemn declaration or affirmation before a court-martial or any court or officer authorised by this Proclamation to administer an oath, wilfully gives false evidence, is guilty of an offence.

Provided always that any civilian who commits any offence mentioned in Sections 27 and 28 may be charged with such offence in a civil court under the relevant sections of the Penal Code or of any Proclamation binding upon civilians.

MISCELLANEOUS MILITARY OFFENCES

29. Any person who uses traitorous or disloyal words regarding Us, is guilty of an offence.

30. Any person who, without due authority, discloses the numbers or positions of any forces, or any magazines or stores thereof, or any preparations for or orders relating to operations or movements of the force, in such a manner as to produce effects injurious to Our service, is guilty of an offence.

31. Any non-commissioned officer who:—

(a) strikes or otherwise ill-treats any soldier;

(b) having received the pay of any officer or soldier, unlawfully detains or unlawfully refuses to pay the same when due, is guilty of an offence.

32. Any person subject to this Proclamation who is guilty of any act, conduct, disorder, or neglect to the prejudice

Scanned by CamScanner

ቃዋሚነት ቍለል የሚል ፤ ወይም በሥራ ላይ ሆኖ ፤ ወይም ሳይሆን የሚሰክር በበደለኛነት ጥፋት ይቀጣል ።

በተለመደው ሕግ የሚያስቀጡ ጥፋቶች ።

፴፫) ማናቸውም ሰው በዚህ አዋጅ የሲቪል ዳኝነቶች ደንብ ተብሎ ከወጣው በዚህ ክፍል ከተመለከቱት አንደኛቸውን ጥፋት የፈጸመ በጦር ሕግ ላይ ጥፋት እንዳጠፋ ተቆጥሮበት በጥፋቱ ወደ ጦር ፍርድ ቤት ቀርቦ ይመረመርና አጥፊ ሆኖ ሲገኝ ከዚህ በታች በተወሰኑት ቅጣቶች ይቀጣል ።

(፩) መንግሥትን በመካድ አጥፊ ሆኖ ሲገኝ የሞት ፍርድ ይፈረድበታል ።

(፪) በነፍስ ግዳይና በቅሚያ ወይም ሴትን በመድፈር ሲፈጸም የነዚህ ቅጣቶች በኢትዮጵያ በወንጀለኛ መቅጫ ደንብ እንደተጻፈው ይቀጣል ፤ ይህም ስለተባለ በሚከተለው አኳኋን ይፈጸማል ።

(ሀ) ማናቸውም በዚህ አዋጅ ውስጥ የሆነ ሰው በጦር ሰዓት የጦር ሥራ ሲሠራ ካልሆነ በተቀር የክሕደትና የነፍስ ግዳይ ፤ የቅሚያ ሴትን የመድፈር ጥፋቶች ቢሠራ ፍርዱ የሚፈጸመው በደንበኛው በሲቪል ፍርድ ቤት ነው ።

(ለ) አንድ ሰው በጦር ሠራዊት ውስጥ ያለ በጦር ሠራዊት ውስጥ ሳይገባ ሊከሰስበት በሚገባ ሲቪል ፍርድ ቤት ሊከሰስ ይቻላል ።

የወታደር አቤቱታ ።

፴፬) አንድ መኰንን ወይም ወታደር ከበላይ መኰንን ደንበኛ ትእዛዝ ሲሰጠው ያለክርክር ፤ ወይም ያለቅርታ በቀጥታ ሊታዘዝ ይገባዋል ። ትእዛዙን ከፈጸመ በኋላ ግን የማይገባ ትእዛዝ ሆኖ ቢሰማው ለሻምበል አዛዥ መኰንኑ አቤቱታውን ሊያደርስ ይችላል ። የሻምበል አዛዡ ካየው በኋላ ደግሞ ነገሩ በደል መስሎ ቢታየው አዛዥ መኰንኑ ዘንድ ለማቅረብ ሊጠይቅ ይችላል ። አዛዥ መኰንኑ ካየው በኋላ እንደዚሁ ደግሞ እንደተበደለ ቢሰማው ከዚያ ለጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንን ሊያመለክት ይችላል ። በጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንንም ወይም በሌለበት በወኪሉ ደስ ያልተሰኘ ሲሆን ከኛ ፊት የንጉሠ ነገሥት ደንበኛ ጦር ሠራዊት በዋና ጠቅላይ አዛዥነታችን በደሉን ለማቅረብ ለመጠየቅ ይችላል ።

ቅ ጣ ቶ ች ።

፴፭) ማናቸውም ሰው ላጠፋው የተለየ ደንብ ስለ ቅጣቱ ያልተወሰነለት በዚህ አዋጅ ላይ በደለኛ ቢሆን ጥፋቱ ሲገለጽ እንደሚከተለው አኳኋን በጦር ፍርድ ቤት እንዲቀጣ ይሆናል ።

(ሀ) ከሐያ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ።

(ለ) ከኛ አገልግሎት በሚያሳፍር ነውረኛነት ማስወጣት

(ሐ) ምክትል ሹም የሆነ እንደሆነ ወደዝቅተኛ ደረጃ ወይም ወደተራ ወታደርነት ማውረድ ፤

(መ) በአካል ቅጣት የሆነ እንደሆነ ከሐያ አምስት በማይበልጥ ግርፋት መግረፍ ፤

(ሠ) ከደመወዝ ማገድ ፤ በገንዘብ መቅጣት ፤ ደመወዝ መቁረጥ ፤

(ረ) በብርቱ መገሠጽ ፤ ወይም ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ቅጣቶች ማናቸውንም አጣምሮ መቅጣት ።

ይህም ከሆነ ፤

of good order and military discipline, or is drunk whether on duty or not, is guilty of an offence.

OFFENCES PUNISHABLE BY ORDINARY LAW.

33. Subject to the provisions of this Proclamation relating to the jurisdiction of the civil courts, any person who shall commit any of the offences in this Article mentioned shall be deemed to be guilty of an offence against military law, and, if charged under this Article with any such offence (in this Proclamation refered to as a civil offence) shall be liable to be tried by court-martial, and on conviction to be punished as follows, that is to say:—

(a) if he is convicted of treason, to be sentenced to death;

(b) if he is convicted of homicide, robbery, or rape, be liable to such penalties as are prescribed in the Penal Code;

Provided as follows:—

(a) a person subject to this Proclamation shall not be tried by a court-martial for treason, murder, robbery, or rape committed in Our dominions unless such person at the time he committed the offence was on active service, but shall be tried by a competent civil court;

(b) a person subject to this Proclamation may be tried by a competent civil court for any offence for which he would be triable if he were not subject to this Proclamation.

COMPLAINTS BY SOLDIERS.

34. When an officer or soldier receives a lawful order from his superior officer, he must obey immediately without demur or hesitation. If after obeying the order he feels that he has a grievance, he may complain thereof to his company commander.

If after seeing his company commander, he still feels aggrieved he may request to see his Commanding Officer.

If after seeing his Commanding Officer, he still feels aggrieved he may complain thereof to the General Officer Commanding the Army. If he is not content with the ruling of the General Officer Commanding the Army or in his absence his representative, he may request that his grievance be laid before Us, as Commander-in-Chief of the Imperial Regular Army.

PUNISHMENTS.

35. Any person who is guilty of an offence under this Proclamation for which no penalty is specially provided shall be liable on conviction by a court-martial to:—

(a) imprisonment not exceeding twenty years;
(b) discharge with ignominy from Our service;
(c) reduction in the case of a non-commissioned officer to a lower grade or to the ranks;
(d) corporal punishment not exceeding twenty-five strokes;
(e) forfeiture, fine or stoppage;
(f) reprimand or severe reprimand;

or to any combination of the above penalties;

Provided that:—

(፩) በዚህ አዋጅ በተወሰነው መጠን በሌላ ቅጣት ላይ መጨመሪያም ቢሆን ወይም ሌላ መቀጫ ሳይታከልበት ጥፋተኛው ሰው ከሚያገኘው ደንበኛ ደመወዙ በመቀነስ ለመቅጣት ይቻላል ።

(፪) የጦር ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ መኰንን በዚህ ክፍል የተመለከተውን የግርፋት ቅጣት የሚፈጸምበትን መሣሪያ በሕግ አድርጎ በጽሕፈት ያስታውቃል ።

(፫) አጥፊው በጦርነት ጊዜ ጥፋት ካላደረገ የግርፋት ቅጣት ሊፈረድበት አይቻልም ። ጥፋቶቹ የተፈጸሙበት በጕዞ ላይ በአገሩ ነዋሪ ሕዝብ ፤ ወይም በንብረታቸው ላይ የሆነ እንደሆነ ግን ግርፋት ይፈረድበታል ።

(፬) አንድ ወታደር በጦርነት ላይ ሳለ ላንድ ጥፋት በደለኛ ቢሆን የጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንን በየጊዜው በሕግ በሚያወጣው የጦር ሜዳ ቅጣት ድንጋጌ መሠረት የጦር ፍርድ ቤቱ እንዲቀጣ ቢያደርግ ከሕግ የተባበረ ይሆናል ። ይኸውም የጦር ሜዳ ቅጣት ተቀጭው ወዲያ ወዲህ እንዳይል በመታገድ በከባድ ሥራ እንዲሆን እንጂ ሕይወትን ወይም አካልን በሚጐዳ ረገድ እንዲቀጣ አይሆንም ።

(፭) ቅጣትን ለማቃለል ከዚህ በላይ የተመለከቱት የጦር ሜዳ ቅጣቶች ከእሥራት በታች የሚለጥቁ ቅጣቶች እንደ መሆናቸው መቆጠር አለባቸው ።

እሥራት ።

፴፮) ከዚህ በታች የተመለከቱት ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ እንደ ተመለከቱት በሚያስቀጡ ጥፋቶች በሚጋለጹ ሰዎች ይፈጸሙባቸዋል ።

(፩) ማናቸውም ሰው በዚህ ዓይነት በተከሰሰ ጊዜ በጦር እሥር ቤት ገብቶ ሊጠበቅ ይቻላል ። ይህም ሲሆን በያንዳንዱ ጊዜ አንድ ጥፋተኛ ይህን በመሰለ በጦር እሥር ቤት ተይዞ በጦር ፍርድ ቤት ነገሩ እንዲመረመር ስብሰባ ሳይደረግ ከስምንት ቀን የበለጠ የሚቆይ ሲሆን ለመቀጠል እንዲዘገይ አስፈላጊ የሚሆንበትን በአዛዥ መኰንኑ አንድ ልዩ ማስታወቂያ እንዲወጣ ይደረጋል ። የጦር ፍርድ ቤት ነገሩን ለመቁረጥ እስቲሰበሰብ ወይም ጥፋተኛው ከእሥራት እስቲለቀቅ አንድ ይህን የመሰለ ማስታወቂያ በየአሥራ አራት ቀን እንዲላክ ይሆናል ።

(፪) የጦር እሥራት ማለት ጥፋተኛውን መያዝ ወይም በእሥራት እንዲጠበቅ ማድረግ ነው ።

(፫) አንድ መኰንን ወይም ምክትል ሹም በጦር ሠራዊት ውስጥ ማናቸውንም ወታደር በጦር እሥር ቤት ውስጥ እንዲገባ ለማዘዝ ይችላል ። ትእዛዙን የሚሰጠው ሰውና እንዲታሠር ትእዛዝ የተሰጠበት ሰው ባንድ ጦር ክፍል ቢሆኑም ባይሆኑም ይህን የመሰለውን ትእዛዝ መቀበል ይገባዋል ።

(፬) አንድ መኰንን ወይም ምክትል ሹም ይህን የመሰለውን ትእዛዝ መቀበል ይገባዋል ። ትእዛዙን የሚሰጠው ሰውና እንዲታሠር ትእዛዝ የተሰጠበት ሰው በአንድ ጦር ክፍል ቢሆኑም ባይሆኑም ፤ ያንድ ጥበቃ አላፊ ምክትል ሹም ወይም ያንድ የጦር ፖሊስ አለቃ ፤ ወይም ረዳቱ ማናቸውም መኰንን ወይም ምክትል ሹም እንዲጠብቅ አንድ ሰው ሲሰጠው ለመቀበል ወይም ለመጠበቅ እንቢ ማለት የለበትም ። ነገር ግን ሰውዬውን ወደ ግዞት ቤት ያገባው የጦር መኰንን ወይም ምክትል ሹም የታሠረበትንና ያጠፋውን ጥፋት ምክንያቱን በጽሕፈት ወይም በቃል እንደተቻለ በቶሎ ወይም በ፳፬ ሰዓት ውስጥ እሥረኛውን እንዲጠ

(i) in addition to or without any other punishment in respect of any offence, an offender may be sentenced to any deduction authorised by this Proclamation to be made from his ordinary pay;

(ii) the General Officer Commanding the Army shall, by regulation, prescribe the instrument with which corporal punishment awarded under this Article shall be inflicted;

(iii) unless the offender be on active service, corporal punishment shall not be awarded except for offences committed on the line of march against the persons or property of inhabitants of the country;

(iv) where a soldier on active service is guilty of any offence, it shall be lawful for a court-martial to award for that offence such field punishment as may be directed by rules to be made from time to time by the General Officer Commanding the Army, and such field punishment shall be of the character of personal restraint or of hard labour but shall not be of a nature to cause injury to life or limb;

(v) for the purpose of commutation of punishment the field punishment above mentioned shall be deemed to stand in the scale of punishments next below imprisonment.

ARREST

36. The following regulations shall be observed with respect to persons when charged with offences punishable under this Proclamation:—

1.) every person when so charged may be taken into military custody:

provided that in every case where any offender remains in such military custody for a longer period than eight days without a court-martial for his trial being ordered to assemble, a special report of the necessity for further delay shall be made by his commanding officer and a similar report shall be forwarded every fourteen days until a court-martial is assembled or the offender is released from custody;

2.) military custody means putting the offender under arrest or putting him in confinement;

3.) an officer or non-commissioned officer may order into military custody any soldier of the army, and any such order shall be obeyed notwithstanding the person giving the order and the person in respect of whom the order is given do not belong to the same corps, arm or branch of the service;

4.) an officer or non-commissioned officer, or non-commissioned officer commanding a guard, or a provost marshal or assistant provost marshal, shall not refuse to receive or keep any person who is committed to his custody by any officer or non-commissioned officer who commits any person into custody to deliver at the time of such committal or as soon as practicable and in every case within twenty-four hours thereafter, to the officer, non-commissioned officer, provost-martial or assistant provost-martial, into whose custody the person is committed, an account either verbal

Scanned by CamScanner

ብቅ ለተሰጠው መኰንን ወይም ምክትል ሹም ፤ ወይም የጦር ፖሊስ አለቃ ወይም ረዳቱ ማስተላለፍ ይገባዋል ።

(፭) ማናቸውም በጦር እሥር ቤት የገባ ሰው የተከሰሰበት ወንጀል አስፈላጊ ያልሆነ መዘግየት ሳይደረግ ነገሩ በደንበኛ ጦር ባለሥልጣን እንዲመረመር በቶሎ ሊቀርብ ይገባዋል ። ቀጥሎም በደለኛውን ለመቅጣት በፍጥነት ወደ ፍርድ ይቀርባል ። አለዚያም ይህ ሰው ከእሥራት መለቀቅ አለበት ።

የአዛዥ መኰንን ሥልጣን ።

፴፯) አዛዥ መኰንን በዚህ አዋጅ አኳኋን ጥፋት አድርጎ የተያዘውን ሰው ነገር ምርመራ ሲያደርግ ሳለ በራሱ ሐሳብ ነገሩን ለመከታተል አስፈላጊ መስሎ ሳይታየው ቢቀር ነገሩን ሊያሻሽልና ሰውዬውን ሊለቅ ይችላል ። ነገር ግን ነገሩ እንዲታይ የሚገባ መስሎ ቢታሰበው ጥፋተኛው በጦር ፍርድ ቤት እንዲቀርብ አስፈላጊውን ማድረግ ይቻላል ። ወይም አንድ ወታደር የሆነ እንደሆነ ባጭሩ ነገሩን ራሱ ሊያየው ይችላል ። ነገሩን በራሱ ዳኝነት የሚያይ ሲሆን ከዚህ በታች እንዳለው ይፈጸማል ።

(፩) አጥፊው አንድ ምክትል ሹም ሳይሆን ተራ ወታደር የሆነ እንደሆነ ፤

(ሀ) ያለፈቃድ ከሥራ በመታጣትና በስካር ጥፋት ምክንያት ካልሆነ በተቀር አዛዥ መኰንኑ ባጥፊው ሰው ላይ ከዚህ በታች ካሉት መቀጫዎች አንዱን ወይም ሌላ ጨምሮ ሊጥልበት ይችላል ።

(፩) አጥፊውን ከአርባ ሁለት ቀን በማይበልጥ እሥራት እንዲታሠር ማድረግ ፤

(፪) አጥፊውን ከጦር ሠራዊት ውስጥ እንዲወጣ ማድረግ ።

(፫) ከአጥፊው ደመወዝ ላይ ከሐያ አንድ ቀን ሒሳብ በማይበልጥ እንዲቆረጥ ማድረግ ።

(፬) አጥፊው ላጠፋው ገንዘብ ወይም ላደረገው ጉዳት መተኪያ ተመዛዛኝ የሆነ ሒሳብ ከደመወዙ እንዲቆረጥ ማድረግ ።

(፭) አጥፊው ከ፳፰ ቀን በማይበልጥ እሥራት እንዲቀጣ ማድረግ ፤ ይህን የመሰለውም እሥራት የተለመደ የወታደርን ሥራ እየፈጸመ በቀን ከአራት ሰዓት በማይበልጥ ለአንድ ጊዜ ከአንድ ሰዓት በማያልፍ በደንበኛ ሥራው ላይ እንዲቀጣ ማድረግ ። እንደዚሁም ደግሞ ማናቸውንም አድካሚ ሥራ እንዲሠራ ማድረግ ።

(፮) አንስተኛ በደሎች ሲሆኑ ፤ ወይም በደንብ ባለመገኘት ሲሆን በጥበቃ ፤ ወይም በሰልፍ ላይ በሚሆንበት ጊዜ ትርፍ የጥበቃዎችና የምርመራዎች ሥራ ጥፋተኛው እንዲሠራ ማድረግ ፤

(፯) በዚህ ክፍል ስለተጠቀሱት ቅጣቶች ምትክ ፤ ወይም በሌላ መቀጫ ላይ ተጨማሪ ሆኖ ከ፳ ግርፋት የማይበልጥ የግርፋት ቅጣት ማድረግ ይችላል ። ይህም ሲሆን በያንዳንዱ የግርፋት ቅጣት በሚደረግበት ጊዜ ወዲያው በጊዜው አዛዥ መኰንኑ ለጦር ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ መኰንን ማስታወቅ አለበት ።

(፰) በጦርነት ሥራ ጊዜ የሆነ እንደሆነ በዚህ አዋጅ በ፴፭ኛው አንቀጽ በ (፬) ቁጥር እንደተመለከተው ዐይነት ከ፳፰ ቀን የማይበልጥ የጦር ሜዳ ቅጣት ይፈረድበታል ።

(፱) በጦር ሥራ ጊዜ በተጨማሪነት ወይም ያላንዳች ሌላ መቀጫ ከተፈረደበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ከሐያ ስምንት ቀን የማይበልጥ ሒሳብ ከደንበኛ ደመወዙ ይቆረጣል።

or in writing of the offence with which the person so committed is charged;

5.) the charge made against every person taken into military custody shall without unnecessary delay be investigated by the proper military authority, and, as soon as may be, either proceedings shall be taken for punishing the offence, or such person shall be discharged from custody.

POWERS OF COMMANDING OFFICER.

37. The Commanding Officer shall, upon an investigation being made of a charge made against a person of having committed an offence under this proclamation, dismiss the charge, if he in his discretion thinks that it ought not to be proceeded with; but where he thinks the charges ought to be proceeded with, he may take steps for bringing the offender to a court-martial or in the case of a soldier he may deal with the case summarily.

Where he deals with the case summarily:—

(1) If the offender is a soldier not being a non-commissioned officer, the commanding officer may:—

A.— save in the case of absence without leave or drunkenness; impose on the offender any one or more of the following punishments:—

(a) award the offender imprisonment for any period not exceeding forty-two days;

(b) dismiss the offender from the Army;

(c) impose a fine not exceeding twenty-one days pay, to be levied by stoppages from the offender's pay;

(d) order the offender to suffer any deduction from his ordinary pay to make good the amount of any loss or damage he may have caused;

(e) order confinement to barracks for any period not exceeding 28 days, such confinement involving the taking of all duties in regular turn, attending parades and punishment drills not exceeding one hour at a time nor four hours in all on the same day, exclusive of ordinary parades, and also liability to employment on duties of fatigue;

(f) order extra guards and pickets, but only for minor offences or irregularities when on or parading for guard or picket;

(g) award corporal punishment not exceeding twenty strokes in lieu of or addition to other punishment under this Article:

Provided that each case in which corporal punishment is awarded shall be reported at the same time by the Commanding Offficer to the General Officer Commanding the Army;

(h) on active service award field punishment within the meaning of Article 35 (iv) of this Proclamation for any period not exceeding twenty-eight days;

(i) on active service, in addition to, or without any other punishment, order that the offender forfeit all ordinary pay for a period commencing on the day of the sentence and not exceeding twenty-eight days.

Scanned by CamScanner

(ለ) ምክትል ሹም ሳይሆን ተራ ወታደር ያለፈቃድ ቀሪ የሆነ እንደሆነ አዛዥ መኰንኑ ነገሩን ባጭሩ አይቶ ከአርባ ሁለት ቀን በማይበልጥ ጊዜ እንዲታሠር ፤ ወይም በጦር ሰፈር በግዞት እንዲቆይ ለማድረግ ይችላል ።

ይህም ሲሆን ለእሥራት የተቆረጠው ቀን ከ፯ ቀን የሚያልፍ ሲሆን ሰውዬው ከሥራ ከጠፋበት ቀን ልክ ሊበልጥ አይገባም ። እንዲሁም ምክትል ሹም ያልሆነ ወታደር በያዳንዱ ከሥራ በቀረበት ቀን ያንድ ቀን ደመወዝ ሒሳብ እንዲያጣ ይሆናል ።

(ሐ) ምክትል ሹም ያልሆነ አንድ ወታደር ሲሰክር አዛዥ መኰንኑ ነገሩን ባጭሩ አይቶ እንደሚከተለው ሊቀጣ ይችላል ።

(፩) በመጀመሪያ ጥፋት ጥፋተኛው እንዲገሠጽ ይሆናል። ወይም በጦር ሰፈር በግዞት እንዲቆይ ይደረጋል እንጂ መቀጫ አይጣልበትም ።

(፪) በሁለተኛውና በያንዳንዱ እያከታተለ በሚያደርገው ጥፋት ቀጥሎ እንዳለው ይቀጣል ።

ከመጀመሪያ ጥፋት ጀምሮ በ፫ ወር ውስጥ ዳግመኛ ጥፋት ቢያደርግ የ፱ ቀን ሒሳብ ደመወዙን ከግዞት ጋር ፤ ወይም ያለግዞት ይቀጣል ።

የመጀመሪያውን ጥፋት ካደረገበት ከሦስት ወራት በኋላ እስከ ፮ ወር ጥፋት ቢያደርግ የ፮ ቀን ሒሳብ ደመወዙን በመቁረጥ ከግዞት ጋር ፤ ወይም ያለግዞት ይቀጣል ።

የመጀመሪያ ጥፋት ከተደረገበት ከ፮ ወር በኋላ እስከ ፱ ወር ጥፋት ቢያደርግ የ፫ ቀን ሒሳብ ደመወዙን በመቁረጥ ከግዞት ጋር ፤ ወይም ያለግዞት ይቀጣል ።

የመጀመሪያው ጥፋት ከተደረገበት ከ፱ ወር በኋላ ቢያጠፋ ለመገሠጽ ፤ ወይም በጦር ሰፈር ግዞት ይቀጣል ።

እነዚህ መቀጫዎች ካጥፊው ሰው ደመወዝ ላይ በመቁረጥ ገቢ ይሆናሉ ።

(፫) ምክትል ሹም ያልሆነ ተራ ወታደር የመጀመሪያውን ጥፋት ካደረገበት ቀን አንሥቶ በ፲፪ ወር ውስጥ አራት ጊዜ በስካር ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝና ነገሩም ተገልጾ በጽሕፈት ገብቶ የተቀጣ የሆነ እንደሆነ በተቆረጠበት መቀጫ ላይ ተጨማሪ የ፫ ቀን ደመወዝ ሒሳብ ይቆረጥበታል ።

(፬) በሥራ ላይ ሆኖ የሚሰክር ወይም በስካሩ ምክንያት ሌላ ጥፋት ያስከተለ በጥፋቱ በዚህ ክፍል በቁጥር (፩) እንደተመለከተው ከሚቆረጥበት ደመወዝ በላይ በእሥራት ወይም በጦር ሰፈር ግዞት እንዲቀጣ ይሆናል ።

(፪) (ሀ) ምክትል ሹም የሆነ እንደሆነ አዛዥ መኰንኑ ከዚህ በታች ከተመለከቱት መቀጫዎች አንደኛውን ወይም ብዙውን ባጥፊው ላይ ሊጥልበት ይችላል ።

(፩) መምከር ፤ በብርቱ መገሠጽ ፤ ወይም ወደ አነስተኛ ማዕርግ ማዋረድ ፤ ወይም በፍጹም ተራ ወታደር ማድረግ፤

(፪) አጥፊውን ከጦር ሠራዊት ውስጥ ማስወጣት ፤

(፫) ከደመወዙ ላይ ከ፳፩ ቀን ከማይበልጥ ሒሳብ መቁረጥ ።

(፬) አጥፊው ያጠፋው ወይም ያበላሸው ተመልሶ እንዲተካ ተመዛዛኝ በሆነ ሒሳብ ከደንበኛ ደመወዙ እንዲጐድል ማድረግ ።

(ለ) ምክትል ሹም ያለስንብት በሚቀርበት በያንዳንዱ ቀን የ፩ ፩ ቀን ደመወዝ እንዲቆረጥበት ሊሆን ይችላል ።

B.—In the case of absence without leave of a soldier not being a non-commissioned officer, the commanding officer may deal with the case summarily and may award imprisonment up to any period not exceeding fortytwo days or confinement to barracks;

Provided that the period of imprisonment awarded, if exceeding seven days, shall not exceed the term of absence.

A soldier not being a non-commissioned officer shall also forfeit one day's pay for every day of absence.

C.—The offence of drunkenness by a soldier not being a non-commissioned officer may be dealt with and summarily punished by the commanding officer as follows:—

(a) for the first offence the offender shall be admonished or confined to barracks, but no fine shall be inflicted;

(b) for the second and every subsequent offence as follows:—
if within three months of the previous offence, by fine to the amount of nine days' pay with or without confinement to barracks; if over three months and within six months of the previous offence, by fine to the amount of six days' pay with or without confinement to barracks;
if over six months and within nine months of the previous offence, by fine to the amount of three days' pay with or without confinement to barracks;
if over nine months of the previous offence, by admonition or confinement to barracks; all such fines to be levied by stoppages from the offender's pay;

(c) where a soldier not being a non-commissioned officer is liable to a fine, and four preceeding instances of drunkenness have been recorded against him within the previous twelve months, an amount of three days' pay shall be added to the amount of the fine imposed;

(d) for an act of drunkenness on duty, or when an act of drunkenness is accompanied by any other offence, the offender may be sentenced, as provided by sub-section (1) of this Article, to imprisonment or confinement to barracks in addition to the fine.

(2) A.— If the offender is a warrant or non-commissioned officer, the commanding officer may impose on the offender any one or more of the following punishments, that is to say he may:—

(a) reprimand, severely reprimand, or reduce any warrant or non-commissioned officer to a lower rank or to the ranks;

(b) dismiss the offender from the Army;

(c) impose a fine not exceeding twenty-one days' pay to be levied by stoppages from the offender's pay;

(d) order the offender to suffer any deduction from his ordinary pay to make good the amount of any loss or damage he may have caused.

B.— A warrant or non-commissioned officer shall also forfeit one day's pay for every day of absence without leave.

Scanned by CamScanner

(ሐ) አንድ ምክትል ሹም ሰክሮ ቢገኝ በዚህ ክፍል በ(፪) (ሀ) የተመለከቱትን መቀጫዎች በዚህ ክፍል በ(፩) (ሐ) ቁጥር በተባለው መቀጫ ላይ ተጨምሮ እንዲቀጣ ይሆናል ።

ያንድ ያነስተኛ ጦር ክፍል አዛዥ መኰንን ሥልጣን ።

፴፰) አንድ ያንስተኛ ጦር ክፍል አዛዥ መኰንን ባንድ ወታደር ላይ የሚቀርበውን ክስ እርግጠኛ ለመሆን መመርመር ይችላል ። ተከሣሹም ጥፋተኛ መሆኑን ከተረዳ በኋላ ከሚለጥቁት ቅጣቶች አንዱን ወይም በተጨማሪ ሊቀጣ ይችላል ።

(፩) ምክትል ሹም ያልሆነ አንድ ወታደር በስካርና ያለ ስንብት ከሥራ መጥፋት ካልሆነ በተቀር በሌላው ጥፋት እንደሚከተለው ሊቀጣ ይችላል ።

(ሀ) ከ፲፬ ቀን በማይበልጥ እሥራት ።

(ለ) ካጥፊው ደመወዝ ከ፲ ቀን ሒሳብ የማይበልጥ መቁረጥ ።

(ሐ) አጥፊው ከ፳፩ ቀን በማይበልጥ እሥራት እንዲቀጣ ማድረግ ፤ ይህን የመሰለውን እሥራት የተለምዶ የወታደር ሥራ እየፈጸመ በቀን ከ፬ ሰዓት የማይበልጥ ላንድ ጊዜ ከ፩ ሰዓት የማያልፍ ፤ እንዲሁ ደግሞ ማናቸውንም አድካሚ ሥራ እንዲሠራ በማድረግ መቅጣት ።

(መ) በሌላ ቅጣት ላይ መጨመሪያም ቢሆን ወይም በዚሁ ብቻ ለመቅጣት ሆነ አጥፊው ያጠፋውንና ጉዳት ያደረገውን እንዲተካ ተመዛዛኝ የሆነ ሒሳብ ከደመወዙ እንዲቆረጥ ።

(ሠ) ስለአነስተኛ በደሎች ፤ ወይም በደንብ ባለመገኘት አጥፊው በሰልፍ ላይ ፤ ወይም በጥበቃ ላይ ሲሆን ትርፍ የጥበቃዎችና የምርመራዎች ሥራ እንዲሠራ ማድረግ ፤

(፪) ምክትል ሹም የሆነ እንደሆነ ፤

(ሀ) ከደንበኛ ደመወዙ ከ፲ ቀን ሒሳብ የማይበልጥ ቀጥቶ ከደመወዙ መቁረጥ ።

(ለ) መገሠጽ ።

(ሐ) ያጠፋውን ፤ ወይም ጉዳት ያደረገውን ነገር እንዲተካ የተመዛዘነ ሒሳብ ከደንበኛ ደመወዙ እንዲቆረጥ ማድረግ ።

(፫) (ሀ) አንድ ወታደር ሲሰክር በ፴፯ አንቀጽ በ(፩) (ሐ) ና በዚህ አዋጅ በ፴፯ አንቀጽ

(፪) (ሐ) በዚሁ መኰንን ነገሩ ባጭሩ ታይቶ ሊቀጣ ይቻላል ።

(ለ) ያለ ፈቃድ ከሥራ በመታጣት የሆነ እንደሆነ በወታደሩ ላይ በ፴፯ አንቀጽ በቍጥር (፩) (ለ)ና በቍጥር (፪) (ለ) የተመለከተው ይፈጸምበታል ።

፴፱) (፩) በዚህ አዋጅ በ፴፯ አንቀጽ እንደ ተወሰነው አዛዥ መኰንኑ የሚስማማ መስሎ እንደታየው ልኩንና ጊዜውን ወስኖ ራሱ ጽፎ ያንድ አዛዥ መኰንን ሥልጣን ላንድ አነስተኛ ጦር ክፍል አዛዥ መኰንን መብት ሊሰጠው ፤ ከሰጠም በኋላ ሊወስድበት ይችላል ። አንድ ምክትል ሹም ከማዕርጉ ለማዋረድና ከሥራውም ለማስወጣት በዚህ ክፍል እንደተባለው አኳኋን የሚደረገው ማናቸውም ፍርድ በአዛዥ መኰንን ፈቃድ ሊሆን ይገባል ።

(፪) ያነስተኛ ጦር ክፍል አዛዥ መኰንን አንድ ወታደር ወይም ተከታዩ የሆነ ያደረገው ጥፋት ከባድ በመሆኑ ምክንያት ወይም አስቀድሞ ላጠፋው ጥፋቱም ከዚህ በፊት በተመለከቱት መቀጫዎች የሚበቃ የተ

C.— A warrant or non-commissioned officer convicted of drunkenness may be fined as laid down in sub-Article (1) (C) of this Article in addition to any of the punishments laid dawn in sub-Article (2) (A) of this Article.

POWERS OF OFFICER COMMANDING A DETACHMENT.

38. Any officer commanding a detachment may examine into the truth of any charge against a soldier, and if his decision is against the accused he may impose on him any one or more of the following punishments:—

(1) if a soldier not being a non-commissioned officer, save in the case of absence without leave or of drunkenness:—

(a) imprisonment for any period not exceeding fourteen days;

(b) fine not exceeding ten days' pay, to be levied by stoppages from the offender's pay;

(c) confinement to barracks for any period not exceeding twenty-one days, such confinment involving the taking of all duties in regular turn, attending parades and punishment drills, not exceeding one hour at a time, nor four hours in all on the same day, exclusive of ordinary parades, and also liability to employment on duties of fatigue;

(d) in addition to or without any other punishment, deduction from ordinary pay to make good the amount of any loss or damage he may have caused;

(e) extra guards and pickets, but only for minor offences or irregularities when on or parading for guard or picket;

(2) If a non-commissioned officer:—

(a) fine not exceeding ten days' pay to be levied by stoppages from the offender's pay;

(b) reprimand;

(c) deduction from his ordinary pay to make good the amount of any loss or damage he may have caused;

(3) A.— The offence of drunkenness by a soldier may be dealt with and summarily punished, as laid down in Article 37 (1) (C) and Article 37 (2) (C) of this Proclamation by such officer.

B.— In the case of absence without leave, the soldier may be dealt with as laid down in Article 37 (1) (B) and Article 37 (2) (B).

39. (1) It shall be lawful for the commanding officer by writing under his hand to confer the powers of a commanding officer, as defined by Article 37 of this Proclamation, on the officer commanding any detachment, under such restrictions and for such period as he may think fit, and to revoke the same. Any sentence of reduction in the case of a non-commissioned officer, and any sentence of dismissal from the service, imposed under this Article, shall be subject to the approval of the commanding officer.

(2) Whenever it shall appear to the officer commanding a detachment that the offence which any soldier has committed would, by reason of its seriousness or by reason of the previous offences of the accused, not be adequately

Scanned by CamScanner

መዘዙ ቅጣቶች በተከሳሹ ላይ አለመደረጉ ፤ የሚሰማው የሆነ እንደ ሆነ ፍርዱን አቆይቶ ሙሉ ራፖርት አዘጋጅቶ ወደ አዛዥ መኰንኑ ያስተላልፋል ። እርሱም አስፈላጊ ሆኖ አንዳች ተጨማሪ ጥያቄ ማድረግ ቢፈልግ ራፖሩን መልሶ ይልካል ፤ ወይም አንዳች ሌላ ወይም ተጨማሪ ትእዛዝ ያደርጋል ። ወይም የሚስማማ መስሎ ቢታየው ነገሩን እንደ ገና ለመስማት ይችላል ።

(፫) በዚህ ክፍል የተመለከተው ማንኛውም የቅጣት ፍርድ በአዛዥ መኰንኑ ፈቃድ ሊማር ይቻላል። ነገር ግን በዚህ ላይ ሊጨመር አይቻልም ።

ያንድ ሻምበልነት አዛዥ መኰንን ሥልጣን ።

፵) ማናቸውም ያንድ ሻምበልነት አዛዥ መኰንን ባንድ ወታደር ላይ የቀረበውን ክስ እርግጠኛ ለመሆኑ ነገሩን መርምሮ ተከሳሹ ጥፋተኛ መሆኑን ሲረዳ ከዚህ በታች ከተመለከቱት ቅጣቶች ባንዱ ፤ ወይም ከአንድ የሚበልጡ ሊቀጣው ይችላል ።

(፩) ምክትል ሹም ያልሆነ አንድ ወታደር ከሥራው በመቅረትና በስካር ምክንያት ካልሆነ በቀር እንደሚከተለው ሊቀጣ ይቻላል ።

(ሀ) ከ፯ ቀን በማይበልጥ ጊዜ በጦር ሰፈር ግዞት ማግባት ።

(ለ) በሰልፍ ላይ በጥበቃ ፤ በዘብ ፤ እነዚህን በመሳሰሉ አነስተኛ ጥፋቶችና በደንብ ባለመገኘት የሆነ እንደ ሆነ ትርፍ የጥበቃና የዘብ ሥራዎች ይጣሉበታል ።

(ሐ) አጥፊው ላበላሸው ነገርና ላደረገው ጉዳት መተኪያ ተመዛዛኝ የሆነ ገንዘብ ከደመወዙ እንዲቆረጥ ይሆናል ።

(፪) አንድ ምክትል ሹም የሆነ እንደ ሆነ መገሠጽ ።

(፫) ያለ ፈቃድ ከሥራ በመታጣት የሆነ እንደ ሆነ በወታደሩ ላይ በ፴፯ አንቀጽ በቍጥር (፩) (ሐ) ክፍልና በ፴፯ አንቀጽ (፪) (ሐ) የተባለው ይፈጸምበታል ።

(፬) በስካር ምክንያት የሆነ እንደሆነ በወታደሩ ላይ በ፴፯ አንቀጽ በቍጥር (፩) (ሐ) በሚለውና በቍጥር (፪) (ሐ) በሚለው እንደተመለከተው ይቀጣል ።

ይህን የመሳሰሉ ሥልጣኖች አዛዥ መኰንኑ የሚገባ መስሎ እንደታየው ለማንኛውም ለጊዜው ላንድ ሻምበልነት አዛዥ ለሚሆን መኰንን ለመስጠት ይችላል ። በዚህ ክፍል ያለው ማንኛውም ቅጣት በአዛዥ መኰንኑ ሥልጣን ሊማር ይችላል ። ነገር ግን ሊጨመር አይቻልም ።

የጦር ፍርድ ቤቶች ።

፵፩) (፩) ስለዚህ አዋጅ ሐሳቦች ሁለት ዐይነት ፍርድ ቤቶች ይቆማሉ ። እነዚሁም ፤

(ሀ) ጠቅላይ የጦር ፍርድ ቤት ።

(ለ) የወረዳ የጦር ፍርድ ቤት ።

(፪) አንድ ጠቅላይ የጦር ፍርድ ቤት በጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንን ጥሪ ስብሰባ ያደርጋል ፤ ወይም በጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ መኰንን ሥልጣን የተሰጠው አንድ መኰንን ጥሪ ሊያደርግና ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል ።

(፫) አንድ የወረዳ ጦር ፍርድ ቤት በወረዳ ጦር ፍርድ ቤቶች ስብሰባ እንዲያደርግ ሥልጣን በተሰጠው አንድ መኰንን ይካሔዳል ። ወይም በጠቅላይ ጦር

punished by any of the aforesaid punishments, or combination of punishments, he shall delay passing sentence and shall report the whole proceedings in the case to the commanding officer, who may send back such report for any further inquiry he considers requisite, or may make any further or other order, or may rehear the case as he may see fit.

(3) Any awards of punishment under this Article shall be subject to any remission the commanding officer may order, but cannot be increased.

POWERS OF OFFICER COMMANDING A COMPANY.

40. Any officer commanding a company may examine into the truth of any charge against a soldier, and, if his decision is against the accused, he may impose upon him any one or more of the following punishments:—

(1) if a soldier not being a non-commissioned officer, save in the case of absence without leave or drunkenness:—

(a) confinement to barracks for any period not exceeding seven days;

(b) extra guards and pickets, but only for minor offences or irregularities when on, or parading for, guard or picket;

(c) deduction from his ordinary pay to make good the amount of any loss or damage he may have caused;

(2) if a non-commissioned officer:—
reprimand;

(3) in the case of absence without leave, the soldier may be dealth with as laid down in Article 37 (1) (C). and Article 37 (2) (C).

(4) In the case of drunkenness the soldier may be dealt with as laid down in Article 37 (1) (C) and Article 37 (2) (C).

Similar powers may at the discretion of the commanding officer, be given to any other officer temporarily in command of a company.

Any awards of punishment under this Article shall be subject to any remmission the commanding officer may order, but cannot be increased.

COURTS-MARTIAL.

41. (1) For the purposes of this proclamation, there shall be two kinds of courts-martial, that is to say:—

(a) general court-martial,

(b) district court-martial.

(2) A general court-martial shall be convened by the general Officer Commanding the Army or some officer deriving authority to convene a general court-martial from the General Officer Commanding the Army.

(3) A district court-martial shall be convened by an officer authorised to convene a district court-martial or some

Scanned by CamScanner

ፍርድ ቤቶች ለስብሰባው ጥሪ እንዲያደርግ ሥልጣን ከተሰጠው አንድ መኰንን የተፈቀደለት አንድ መኰንን የወረዳውን የጦር ፍርድ ቤት በጥሪ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል ።

(፬) ጠቅላይ የጦር ፍርድ ቤት ከአምስት የማያንሱ መኰንኖች ይቀመጡበታል ። እነርሱም በእኛ አገልግሎት ውስጥ እያንዳንዳቸው ከ፫ ዓመት የማያንስ ዘመን የሹመት ማዕርግ የያዙ መሆን አለባቸው ። ነገር ግን በመንግሥት ሥራ ምክንያት አምስት መኰንኖች ለማግኘት የማይቻል ቢሆን ሰብሳቢው መኰንን በዚህ ረገድ በርሱ ፕሬዚዳንትነት የጦር ፍርድ ቤቱ በ፫ መኰንኖች ሊካሔድ ይችላል ።

(፭) የወረዳ የጦር ፍርድ ቤት ከሦስት በማያንሱ መኰንኖች ሊካሔድ ይገባል ። እነዚሁም እያንዳንዳቸው በኛ አገልግሎት ውስጥ ከሁለት ዓመት የማያንስ ዘመን የሹመት ማዕርግ ያላቸው መሆን አለባቸው ።

(፮) አንድ ጠቅላይ የጦር ፍርድ ቤት የሞት ፍርድና አነስተኛ የሆነውን ማንኛውንም በዚህ አዋጅ የተመለከተውን ቅጣት ሁሉ ለመፍረድ ሥልጣን አለው ። ይህም ስለ ሆነ በጦር ፍርድ ቤቱ ከአምስት የማያንሱ አባሎች በቲቀመጡ ጊዜ የሁሉም ሐሳባቸው አንድ ካልሆነ በማንኛውም እሥረኛ ላይ የሞት ፍርድ ሊፈረድ አይቻልም ።

(፯) የወረዳው የጦር ፍርድ ቤት የሞት ፍርድና ከሁለት ዓመት የሚበልጥ እሥራት መቁረጥ አይችልም ። ነገር ግን አስቀድሞ እንደተባለው ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩትን ጥፋቶች ያደረገ በወረዳ ጦር ፍርድ ቤት ነገሩ ሊታይና ሊቀጣ ይቻላል ።

(፰) ያንድ የጦር ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በባለ ሥልጣኑ ሰብሳቢ ትእዛዝ ሊሾም ይቻላል ። የወረዳ የጦር ፍርድ ቤት የሆነ እንደሆነ ግን ለዳኝነቱ ሰብሳቢ የሆነው መኰንን ራሱ በፕሬዚዳንትነት ሊሠራ ይችላል ።

(፱) የተቻለ እንደሆነ በጦር ፍርድ ቤት ከተቀመጡት አባሎች አንደኛው መኰንን ተከሳሹ ከሚያገለግልበት ባታዮን ውስጥ እንዲሆን ሌሎቹ ግን የየሌላው የጦር ሠራዊት ክፍል መኰንኖች እንዲሆኑ ይገባል ።

<u>የጦር ሜዳ ጠቅላይ የጦር ፍርድ ቤቶች ።</u>

፵፪) (፩) ለማንኛውም አነስተኛ ጦር ክፍል ለሚያዝ መኰንን ወይም በጦርነት ጊዜ ከፍተኛ ጦር ክፍል ለሚያዝ መኰንን ወይም ይህን ለመሳሰሉ ልዩ ልዩ ዐይነት የጦር ክፍሎች በጦርነት ሥራ ላይ ለሚያዙ መኰንኖች አንድ ሰው ጥፋት በማድረጉ ማመልከቻ ቢቀርብላቸው መኰንኑ በሐሳቡ ጥፋቱን በተለመደው ጠቅላይ የጦር ፍርድ ቤት ለማየት የማይሆን መስሎ ቢታየው ምንም ጠቅላይ ጦር ፍርድ ቤት ለዳኝነት ለመሰብሰብ ሥልጣን ባይኖረው በዚህ አዋጅ የጦር ሜዳ ጠቅላይ ጦር ፍርድ ቤት ማቆምና አጥፊው እንዲቀጣ ማድረግ ይቻላል ። ይህም ስለተባለ ፤

(ሀ) ያንድ የተነጠለ የወታደሮች ክፍል በጦርነት ላይ ያልሆነ አዛዥ መኰንን ጥፋተኛው ሰው በርሱ ታዛዥነት ውስጥ ካልሆነ በቀርና ተከሳሹ ያጠፋው ጥፋት ባገሩ ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች ላይ ፤ ወይም በንብረ

other officer deriving authority to convene a district court-martial from an officer authorised to convene general courts-martial.

(4) A general court-martial shall consist of not less than five officers each of whom must have held a commission in Our service of not less than three years, unless the officer convening the court-martial is of opinion that five officers are not available, having due regard to the public service, in which case the court-martial may consist of three officers, in which case also the convening officer may preside.

(5) A district court-martial shall consist of not less than three officers, each one of whom must have held a commission in Our service for not less than two years.

(6) A general court-martial shall have power to try all persons and to pass sentence of death or such less punishment as in this proclamation mentioned:

Provided that if the court-martial consists of less than five members, sentence of death shall not be passed on any prisoner without the concurrence of all the members.

(7) A district court-martial shall not award the punishment of death or of imprisonment in excess of two years, but, subject as aforesaid, any offence under this Proclamation committed by a person may be tried and punished by a district court-martial.

(8) The president of a court-martial shall be appointed by order of the authority convening the Court and, in the case of a district court-martial, the convening officer may appoint himself as president.

(9) One of the members of the court shall, if possible, be an officer of the battalion in which the person accused is serving, and the other members of the court may be officers of other units of the army.

FIELD GENERAL COURTS-MARTIAL.

42. (1) Where a complaint is made to any officer in command of any detachment or portion of troops or to the commanding officer of any corps or portion of a corps on active service, or to any officer in immediate command of a body of forces on active service, that an offence has been committed by any person, then, if in the opinion of such officer it is not practicable that such offence should be tried by an ordinary general court-martial, it shall be lawful for him, although not authorised to convene general courts-martial, to convene a court-martial in this proclamation referred to as a field general court-martial, for the trial of the person charged with such offence:

Provided as follows:—

(a) an officer in command of a detachment or portion of troops on active service shall not convene a field general court-martial for the trial of any person unless that person is under his command, nor unless the offence with which the person is

ታቸው ካልሆነ በተቀር የሰውዬውን ጥፋት ለማየት አንድ የጦር ሜዳ ጠቅላይ ጦር ፍርድ ቤት ስብሰባ ማድረግ አይችልም ።

(ለ) አንድ የጦር ሜዳ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኝነት ለማየት ከ፫ መኰንኖች ያነሰ ሊሆን አይገባም ። ነገር ግን በመንግሥት ሥራ ምክንያት በሐሳቡ ሦስት መኰንኖች ለማግኘት የማይቻል መሆኑን ሲረዳ በሁለት መኰንኖች ሊካሔድ ይችላል ።

(ሐ) በዚህ የጦር ፍርድ ቤት ሰብሳቢው መኰንን ፕሬዚዳንት ለመሆን ይችላል ። ነገር ግን እርሱ እንደ መሰለው ከካፒቴን ማዕርግ በታች አይሁን እንጂ ሌላ ማንኛውንም የሹመት ማዕርግ ያለውን መኰንን ፕሬዚዳንት እንዲሆን ሰብሳቢው የሚስማማ መስሎ የታየውን መኰንን ለመምረጥ ይችላል ።

(መ) ከሦስት ያነሡ መኰንኖች በተቀመጡበት ጊዜ የጦር ሜዳ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚፈርደው ቅጣት ወይም እሥራት በዚሁ አዋጅ ከተፈቀደው የጦር ሜዳ ቅጣት ሊበልጥ አይቻልም ።

(፪) በዚህ አዋጅ በ፵፩ አንቀጽ በተመለከተው ውስጥ ከ፱ኛው ቊጥር በስተቀር ሌላው በጦር ሜዳ ጠቅላይ ጦር ፍርድ ቤት አይፈጸምም ። ነገር ግን የሞት ፍርድ ሲሆን ሁሉም አባሎች በአንድነት ተሰብስበው በነገሩ ሳይከራከሩበት የጦር ሜዳ ጠቅላይ ጦር ፍርድ ቤት በማንኛውም እሥረኛ ላይ የሞት ፍርድ ሊፈርድበት አይገባም ።

(፫) በዚህ አዋጅ በጦር ፍርድ ቤት እንዳይታይ ከተወሰነው ጥፋት በቀር አንድ የጦር ሜዳ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማንኛውንም የዳኝነቱን ሥራ በሚመራው መኰንን ታዛዥነት ውስጥ ያለውን ሰውና በዚህ ክፍል የተመለከተውን ማንኛውንም ጥፋት ያጠፋውን ሰው ነገሩን ለመመርመርና ለመፍረድ እንደ ጠቅላይ የጦር ፍርድ ቤት ሙሉ ችሎታ አለው ። ይህም ሲሆን ዘወትር ይህን የመሰለ የጦር ፍርድ ቤት ፍርድ በዚህ አዋጅ እንደተወሰነው ካልጸና በተቀር አይፈጸምም ።

፵፫) (፩) ከዚህ በታች የሚከተሉት ባለሥልጣኖች ተመርምሮ የተገኘውን ነገርና በጦር ፍርድ ቤት የተፈረደውን ፍርድ ለማጽናት ሥልጣን አላቸው ።

(ሀ) በወረዳ የጦር ፍርድ ቤት የሆነ እንደ ሆነ ተመርምሮ የተገኘው ነገር በቀረበለት ቀን ይህን የመሰለው የጦር ፍርድ ቤት ሰብሳቢ ባለሥልጣን ሊፈርድና ሊያጸና ይችላል ። ይህም ሲሆን የእሥራት ፍርድ የሆነ እንደ ሆነ የእሥራቱ ጊዜ ከ፮ ወር አይበልጥም ፤ የእሥራቱ ፍርድ ከ፮ ወር የሚበልጥ የሆነ እንደ ሆነ ፍርዱ በጦር ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ መኰንን ወይም ባንድ በሌላ በጠቅላይ ጦር ፍርድ ቤት የተመረመሩትንና የተፈረዱትን ነገሮች ሊያጸና ሥልጣን በተሰጠው መኰንን ይጸናል ።

ያንድ የጦር ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በዚያ በጦር ፍርድ ቤት የተመረመረውን ወይም የተፈረደውን ሊያጸና ሥልጣን የለውም ። በጦር ፍርድ ቤቱ ተመርምሮ የተገኘውን ነገር ወይም የተፈረደውን ፍርድ ወደ ጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንን ፤ ወይም ከጠቅላይ

charged is an offence against the property or person of an inhabitant of or resident in the country in which the offence is alleged to have been committed;

(b) a field general court-martial shall consist of not less than three officers, unless the officer convening the same is of the opinion that three officers are not available having due regard to the public service in which case the court-martial may consist of two officers;

(c) the convening officer may preside; but he shall whenever he deems it practicable appoint another officer as president, who may be of any rank, but shall, if practicable in the opinion of the convening officer, be not below the rank of captain;

(d) where a field general court-martial consists of less than three officers, the sentence shall not exceed such field punishment as is allowed by this proclamation, or imprisonment.

(2) Nothing in Article 41 of this Proclamation, except sub-Article (9) thereof, shall apply to a field general court-martial but sentence of dealth shall not be passed on any prisoner by a field general court-martial without the concurrence of all the members.

(3) A field general court-martial may, notwithstanding the restrictions enacted by this proclamation in respect of any trial by court-martial of civil offence within the meaning of this Proclamation try any person who is under the command of the convening officer, and is charged with any such offence as is mentioned in this Article, and may award for such offence any sentence which a general court-martial is competent to award for such offence;

Provided always, that the no sentence of any such court-martial shall be executed until confirmed as provided by this Proclamation.

43. (1) The Following authorities shall have power to confirm the findings and sentences of courts-martial, that is to say:—

(a) in the case of a district court-martial, the officer having authority to convene such a court-martial at the date of the submission of the finding and sentence thereof;
Provided that, in the case of a sentence of imprisonment being passed, the period of imprisonment does not exceed six months; if the sentence of imprisonment exceeds six months, it shall be confirmed by the General Officer Commanding the Army, or by some officer having authority from him to confirm the findings and sentences of general courts-martial;

Provided further that the president of a court-martial shall not have authority to confirm the finding or sentence of that court-martial; but shall refer the finding and sentence of that court-martial to the General Officer Commanding the Army

Scanned by CamScanner

አዛዥ መኰንን መርምሮ ለማጽናት ሥልጣን ወደ ተሰጠው መኰንን ያስተላልፋል ።

(ለ) ያንድ ጠቅላይ የጦር ፍርድ ቤት የሆነ እንደ ሆነ የጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንን ወይም በጠቅላይ ጦር ፍርድ ቤቶች የተመረመሩትንና የተፈረዱትን ለማጽናት ከርሱ ሥልጣን የተሰጠው መኰንን ነገሩን አጣርቶ ያጸናል ።

(ሐ) ያንድ የጦር ሜዳ የጦር ፍርድ ቤት የሆነ እንደ ሆነ ጥፋቶቹ የተፈጸሙበት የጦር ክፍል ወይም የወታደሮቹ ክፍል ለዳኝነት ሰብሳቢው መኰንን በጠቅላይ ጦር ፍርድ ቤት የተመረመሩትንና የተፈረዱትን ነገሮች ለማጽናት ሥልጣን ከተሰጠው መኰንን ጋር ነገሩን ለማጣራትና ለማረጋገጥ ይችላል ።

(፪) ነገሩን አጣርቶ የሚያጸናው ባለሥልጣን ማንኛውም የጦር ፍርድ ቤት የፈረደውን ነገር ሲያጸና አጥፊው በጦር ፍርድ ቤት የተፈረደበትን ለመሻሻል ፤ ወይም ይቅርታ ለማድረግ ፤ ወይም ባነስተኛ ቅጣት ፤ ወይም ቅጣቶች ሊለውጥ ይችላል ።

(፫) በነጻ ለመለቀቅ ሲሆን በዚህ አዋጅ እንደ ተወሰነው አኳኋን አንድ የጦር ፍርድ ቤት የመረመረውና የፈረደው አይጸናም ። ነገር ግን ነገሩን አጣርቶ ለማጽናት ሥልጣን ያለው ያንኑ ካላጸናው በተቀር ።

(፬) የሞት ፍርድ በዚህ አዋጅ አስፈላጊ በሆነ በሌላ አኳኋን እንዲረጋገጥ እንደ ታዘዘው ካልተረጋገጠና እኛም ካላጸናነው ሊፈጸም አይቻልም ።

(፭) ባንድ የጦር ፍርድ ቤት ከ፮ ወር የማይበልጥ እሥራት የተፈረደ እንደሆነ በዳኝነት ተመርምሮ የተገኙት ነገሮች ወደ ጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንን እንዲተላለፉ ይሆናል ።

(፮) ባንድ ጦር ፍርድ ቤት የተፈረደው ፍርድ የጸና እንደሆነ የጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንን በአጥፊው ሰው ላይ የተፈረደውን የቅጣት ፍርድ ሊያቃልልለት ወይም ይቅርታ ሊያደርግለት ፤ ወይም ለውጡን አነስተኛ ቅጣት ሊያደርግለት ሥልጣን አለው ።

የፍርድ አፈጻጸም ።

፵፬) (፩) በማንኛውም ሰው ላይ የተፈረደው የእሥራት ፍርድ በኢትዮጵያ ውስጥ በቆመው በማንኛውም የጦር ወይም የሲቢል እሥር ቤት ሊፈጸም ይችላል ። ወይም የእሥራት ፍርድ ከአርባ ሁለት ቀን የማይበልጥ የሆነ እንደ ሆነ የጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንን ለዚህ ሐሳብ የሚስማማ መስሎ በታየው ጦር ሠፈር ወይም ምሽግ በቤት ውስጥ ፤ ወይም በጨለማ ቤት ውስጥ እንዲታሰር ሊያደርግ ይችላል ። የጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ እነዚህን በመሰሉ እሥር ቤቶችና ጨለማ ቤቶች ውስጥ ስለሚገቡት እሥረኞች በእሥራት አገባብ ፤ አፈታት ፤ አጠባበቅ ፤ አዘዋወር ፤ የዘብ አጠባበቅ ፤ ምግብ ፤ ከባድ ሥራ ፤ ሞያ ፤ ሥርዓት ፤ አስተዳደር ፤ ትምህርት ፤ ስለማንኛውም ጥፋቶችና ሌላዎችም ፤ በማንኛውም ይህን የመሳሰሉ እሥራትና እሥር ቤቶች አስተዳደርና አፈጻጸም ፤ አልፎ አልፎ ሕግ ማውጣት ይችላል ።

ይህም ስለ ሆነ ከዚህ በላይ የተባለው ደንብ እስኪወጣ ድረስ ማንኛውም ሰው ይህን በመሰለ እሥር ቤትና የማቆያ ፤ ወይም የጨለማ ቤት ውስጥ ገብቶ እን

or to some officer having authority from him to confirm the findings and sentences of courts-martial;

(b) in the case of a general court-martial, the General Officer Commanding the Army or some officer deriving authority from him to confirm the findings and sentences of general courts-martial;

(c) in the case of a field general court-martial, an officer having authority to confirm the findings or sentence of general courts-martial for the trial of offences in the force of which the detachment or portion of troops under the command of the convening officer forms part.

(2) The confirming authority may, when confirming the sentence of any court-martial, mitigate or remit the punishment thereby awarded, or commute such punishment for any less punishment or punishments to which the offender might have been sentenced by the said court-martial.

(3) Subject to the provisions of this Proclamation with respect to the finding of acquittal, the finding and sentence of a court-martial shall not be valid except in so far as the same may be confirmed by an authority authorised to confirm the same.

(4) Sentence of death shall not be carried into effect unless in addition to the confirmation otherwise required by this Proclamation, it is approved by Us.

(5) When the sentence imposed by a court-martial exceeds six months imprisonment the proceedings of the court shall be forwarded to the General Officer Commanding the Army.

(6) When a sentence passed by a court-martial has been confirmed, the General Officer Commanding the Army shall have power to mitigate or remit the punishment thereby awarded, or to commute such punishment for any less punishment or punishments to which the offender might have been sentenced by the said court-martial.

EXECUTION OF SENTENCES

44. (1) Any sentence of imprisonment imposed upon any person may be carried out in any military or civil prison established within Our Empire, or, where the sentence of imprisonment imposed does not exceed forty-two days, in any lock-up house or cells which for that purpose the General Officer Commanding the Army may think fit to attach to any fort or barracks. The General Officer Commanding the Army may from time to time make regulations for the government of such prisons and of any lock-up house or cells attached by him to any fort or barracks, and with regard to the admission, discharge, custody, removal, safeguarding, diet, labour, occupation, discipline, instruction and offences of any persons confined therein, and with regard to any and every other matter relating to and connected with the carrying out and management of imprisonment in any such prison, lock-up house or cells;

Provided that no persons shall be imprisoned in any such prisons, lock-up house, or cells until such regulations as aforesaid shall have been made and provided that any per

Scanned by CamScanner

ዲታሠር አይሆንም ። ግን የተፈረደበት ሰው የእሥራቱ ፍርድ ከአርባ ሁለት ቀን በላይ የሆነ እንደሆነ ወደ እሥር ቤት እስቲሔድ ድረስ ለጊዜው በነዚህ እሥር ቤቶች ውስጥ እንዲቆይ ለማድረግ ይችላል ።

(፪) ማንኛውም ከዚህ ከተሰጠው ደንብ አኳኋን ፍርዱን የተቀበለው ሰው የወታደርነቱን ሥራ በመልቀቅ ፤ ወይም በሌላ አኳኋን ከዚህ አዋጅ ውስጥ እውጭ የሚሆን ቢሆንም የተፈረደውን ፍርድ ከመፈጸም የሚያግድ ነገር የለም ።

(፫) ማንኛውም የወህኒ ቤት ጠባቂ በዚህ አዋጅ እንዲታሠር የተፈረደበትን ማንኛውንም ሰው ሁሉ በአዛዥ መኰንን ትእዛዝ ፤ ወይም ፍርዱን በፈረደው መኰንን ትእዛዝ የእሥረኛውን ጥፋትና የሚታሠርበትንም ጊዜ ልክ ወስኖ ያስተሳሰሩንም አኳኋን በዝርዝር ጽፎ በጽሕፈት ማዘዣ በታዘዘ ጊዜ እሥረኛውን ተቀብሎ በእሥር ቤት አግብቶ ፍርዱን ያስፈጽመዋል ።

(፬) ማንኛውም ሰው እንደዚህ ያለ አንዳች ፍርድ ተፈርዶበት እሥር ቤት ገብቶ የሚፈጽም እንደ ወንጀለኛ ሰው ሊታይና በወንጀለኛ ቅጣት እሥረኛ አኳኋን እንዲታሠር ይሆናል ።

፵፭) (፩) ማንኛውም ወታደር በአንዳች ቀን በመክዳት ያለስንብት በመታጣት የእሥራት ፍርድን ለመፈጸም ወይም የጦር ሜዳ ቅጣትን ፤ ወይም በአንዳች ፍጻሜ በሚያስፈርድበት ጥፋት በሲቢል ፤ ወይም በጦር ፍርድ ቤት ለምርመራ በመጠበቅ በመቆየት ቀሪ ቢሆን ደመወዙ የተገባው ሊሆን አይቻልም ።

(፪) ይህን በመሰለ ከሥራ መጥፋት ፤ ወይም በእሥራት ፤ ወይም በማቆያ ቤት በመቆየት ባንድ ቀን ውስጥ ፤ ወይም ግማሽ ጊዜ በአንድ ቀን ግማሽ በሌላው ቀን ታስቦ ፮ ሰንት ፤ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ጊዜ በመታጣት በእሥራት ፤ በመቆያ ቤት በመሆን ሲቀር ስለ አንድ ቀን መጥፋት ይታሰባል ። ይህም ስለሆነ አንድ ወታደር ከሥራ በመታጣት ፤ ወይም በመታሠር ፤ ወይም በጦር ሜዳ ቅጣት ሆነ ፤ ወይም በመቆያ ቤት ሆኖ ሳለ ሥራውን ከመፈጸም ቢተጓጐልና ሥራውም በሌላ ባንድ ሰው የተጣለ ሲሆን ፤ በዚህ አኳኋን የቀረበት ከ፮ ሰዓት ያነሰ ጊዜ እንኳ ቢሆን ስለ አንድ ቀን ቀሪነት ይቈጠራል ።

፵፮) (፩) በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጥፋቶች ምክንያት በወታደሮቹ ላይ የሚጣሉት የገንዘብ መቀጫዎች ገቢ የሚሆኑት ጥፋት በፈጸመበት ጊዜ አጥፊው ከሚያገኘው ደመወዝ ላይ ፤ ወይም ከዚያ በኋላ ከሚታከለለት ላይ ነው እንጂ ከሌላ ሒሳቡ ወይም ከሌላ ስፍራ አይደለም ።

(፪) የገንዘብ መቀጫዎችን ለመጣል ሥልጣን ያላቸው መኰንኖች እንደመሰላቸው በሥልጣናቸው ከደመወዝ የሚቆረጠውን የገንዘብ ልክ ይወስናሉ ። በማናቸውም ምክንያት ከአጥፊው ሰው በወር ከሚያገኘው ደመወዝ ግማሽ ይበልጥ አይነካም ። ባንድ ሰው ላይ ካንድ ማዘዣ በላይ የቀለብ ማቆሚያ ብዙ ማዘዣዎች በተላለፉም ጊዜ ቢያንስ ቢያንስ ከወር ቀለቡ ግማሹ ቀሪ ሁኖለት ቀለቡ ተቆራጭ ይሆናል ።

(፫) ባንድ ሰው ላይ ከአንድ ጊዜ የበለጠ ደመወዙ እንዲቆረጥ በመደጋገም ትእዛዞች በተሰጡ ጊዜ አስፈ

son, notwithstanding that his sentence exceeds forty-two days, may, whilst awaiting removal to a prison, be temporarily imprisoned in any such lock-up house or cells.

(2) A sentence passed upon any person shall be in no respect affected by such person ceasing to be subject to this Proclamation by discharge or otherwise.

(3) Every gaoler shall receive into his custody and carry out the sentence upon any person sentenced to imprisonment for any offence under this Proclamation, upon an order in writing in that behalf being delivered to him under the hand of the commanding officer or of the officer imposing the sentence, which order shall specify the offence and the period and description of imprisonment.

(4) Every person whilst undergoing any such sentence of imprisonment shall be deemed to be and be dealt with as a criminal prisoner.

45. (1) No pay shall accrue or become due to any soldier in respect of any day during which he is absent on desertion or without leave or undergoing any sentence of imprisonment, or field punishment, or is under detention awaiting any trial by a civil court or court-martial which results in his conviction for any offence or is on a charge of absence without leave for which he is afterwards awarded imprisonment or field punishment by a competent authority.

(2) Any such period of absence or imprisonment or field punishment or detention lasting six hours or upwards, whether wholly in one day, or partly in one day and partly in another, may be deemed for the purpose of this Article to constitute a day of absence or a day of imprisonment or of detention:

Provided that where the soldier has been thereby prevented from fulfilling any military duty which was consequently thrown upon some other person, any such period of absence or imprisonment or field punishment or detention may for the purpose of this Article be deemed to constitute a day notwithstanding that the duration thereof was less than six hours.

46. (1) All fines imposed upon soldiers for offences under this Proclamation shall be recovered by stoppages from the offender's pay due at the time of committing such offence, or thereafter accuring due, and not from any other source in any other manner.

(2) The amount of stoppages shall be in discretion of the officers authorised to impose fines, in no case exceeding one-half of the monthly pay of the offender: and whenever more than one order of stoppage for any cause is in force against the same person, so much only of his pay shall be stopped as shall leave him a residue of at least one-half of his monthly pay.

(3) When more than one order of stoppage is made upon the same person the order or orders later in date shall,

Scanned by CamScanner

ላጊ የሚሆን የሆነ እንደሆነ ተቀዳሚዎቹ ተከፍለው እስቲጨረሱ የኋለኞቹ እንዲቆዩ ይሆናሉ ።

፵፯) (፩) በግዛታችን ውስጥ ከወታደሮች ወይም ከተከታዮቻቸው ላይ በመቀጫዎች ምክንያት የሚገባው ገንዘብ ለጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንን ተከፍሎ «የጦር መቀጫዎች ገንዘብ» ተብሎ በሚታወቅበት ረገድ ገቢ ሆኖ ሊቀመጥ ይገባል ።

(፪) ከጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንን ፈቃድ በተቀር ከጦር መቀጫዎች ገንዘብ ላይ አንዳች ወጭ ለማድረግ አይቻልም ።

(፫) የጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንን በአንድ አዛዥ መኰንን አሳሳቢነት ከዚህ በታች ለተመለከቱት ሐሳቦች ከጦር መቀጫዎች ገንዘብ ላይ ወጭዎች እንዲደረጉ ለመፍቀድ ይቻላል ።

(ሀ) ለሞቱ ወታደሮች ሚስቶች ወይም ቤተ ሰቦች ወይም የጦር ሥራ ባለመቻል ለወጡትና ከችግር ላይ ለወደቁ ወታደሮች እርዳታ ።

(ለ) ስለአትሌቲክ ጨዋታዎችና ሌላም ይህን በመሰለ ለተመሠረቱት ነገሮች ወይም ስለ ጦር ሠራዊቱ ወታደሮች ጠቀሜታ በሚሆን ነገር ለሽልማት መክፈል

(ሐ) የጠመንጃ ተኩስን ለማበረታት ለጥይቶች መግዣ ።

(መ) ለጦር ሠራዊት የሚሆን ዕቃ ለማስገኛ ዋጋው በሌላ አኳኋን ከጦር ሠራዊት ገንዘብ ለመክፈል የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ።

(ሠ) አንድ የከዳን ሰው ለሚይዝ ፤ ወይም ለሚይዙ እንደ አንድ ሽልማትና ላዲስ ምልምል ወታደር እንደ ሽልማት የሚሰጥ ።

(ረ) የሆነውን ዘመን ያህል በወታደር አገልግሎት ደንብ ውስጥ ሲያገለግሉ ቆይተው ለሚወጡ ወታደሮች ተመልሰው በሰልፍ ውስጥ ሲገኙ የኒሻን ሪቦን ለማስገኛ ።

(፬) ከጦር መቀጫዎች ገንዘብ ሒሳብ የደረሰኞችንና የወጭን ማስታወቂያዎች አዛዥ መኰንኑ ለጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንን ማስረከብ አለበት ።

ስለ ሥርዓት ተጨማሪ ደንቦች ።

፵፰) በማንኛውም ጥፋት አንድ ምክትል ሹም የሚቀጣ ሲሆን አስቀድሞ ከሹመቱ ወደ ተራ ወታደርነት ካልወረደ በተቀር የግርፋት ወይም የእሥራት ቅጣት ሊፈረድበት አይቻልም ።

፵፱) በጉዞ መሥመር ላይ ፤ ወይም በጦርነት ውስጥ ካልሆነ በተቀር የግርፋት ቅጣት ከተፈረደ በኋላ ፳፬ ሰዓት ሳያልፍ ፍርዱ ሊፈጸም አይቻልም ።

ስለመቀጠርና ከሥራ ስለማሰወጣት ፤ ስለአገልግሎትም ።

፶) (፩) ማንኛውም ወታደር ከጸሐፊና ከሐኪም ቤት ሠራተኞች ፤ ከለጓሚዎች ፤ ከጠራጊዎች በተቀር ለመጀመሪያ ጊዜ በጦር ሠራዊት ውስጥ ፯ ዓመት ለማገልገል ቃል ገብቶ ይቀጠራል ።

(፪) ጸሐፊዎች ፤ የሐኪም ቤት ሠራተኞች ፤ ጠራጊዎች ላጓሚዎች የጦር ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ መኰንን በየጊዜው እንደሚወስነው ዘመን ይቀጠራሉ ።

if necessary, be postponed as to their enforcement until the earlier orders are discharged.

47. (1) All fines recovered within Our Empire from soldiers shall be paid over to the General Officer Commanding the Army to be placed to the credit of a fund to be styled the "Military Fines Fund."

(2) No payment shall be made from the Military Fines Fund except on the authority of the General Officer Commanding the Army.

(3) The General Officer Commanding the Army on the recommendation of a commanding officer may sanction payments from the Military Fines Fund for any of the following purposes, namely:—

(a) assistance to the wives or families of deceased soldiers, or soldiers discharged as invalids, who may be in immediate want;

(b) contributions towards prizes to be given at athletic meetings and similar events organized by or for the benefit of the soldiers of the army;

(c) purchase of ammunition for the encouragement of rifle shooting;

(d) provision of any articles for the use of the army when the cost of such provision cannot be met otherwise out of army funds;

(e) as a reward to the apprehender or apprehenders of a deserter, and as a reward for recruiting;

(f) provision of medal ribbons for discharged soldiers who are attending a parade as such.

(4) Annual statements of receipts and expenditure on account of the Military Fines Fund shall be rendered by the commanding officer to the General Officer Commanding the Army.

SUPPLEMENTARY PROVISIONS AS TO DISCIPLINE.

48. The sentence on a non-commissioned officer for any offence shall in no case include corporal punishment or imprisonment unless it also includes reduction of the offender to the rank of a private.

49. No sentence of corporal punishment shall be carried out until a period of twenty-four hours has elapsed since the award, except on the line of march or on active service.

ENLISTMENT, DISCHARGE AND SERVICE.

50. (1) every soldier other than a clerk, medical orderly, syce, or sweeper shall be enlisted for a first term of engagement to service in the army of seven years.

(2) Clerks, medical orderlies, syces and sweepers shall be enlisted for such terms as may from time to time be fixed by the General Officer Commanding the Army.

Scanned by CamScanner

፶፩) ማንኛውም ሰው ከአገልግሎት ሲለቅ ፤ ወይም እንደገና በስምምነት ሲቀጠር የአገልግሎት ዘመን ሲታሰብ ከዚህ በታች በተመለከቱት ምክንያቶች ቀሪ የሆነባቸው ቀኖች ሒሳብ አይገቡም ፤

(ሀ) ፍጻሜው ነጻ የሚለቀቅበት ፤ ወይም እሥረኛው እንዲወጣ የሚሆንበት ምክንያት ለምርመራ በእሥራት ከቆየበት በተቀር ማንኛቸውም በእሥራት የቆየበት ቀን ፤

ለ) በማንኛውም ጊዜ የኮበለለበት ፤

ሐ) ከ፵፰ ሰዓት በላይ ያለ ስንብት ከሥራው የታጣበት ጊዜያት ፤

፶፪) (፩) ማንኛውም መልካም ጠባይ ያለው ወታደር በጦር ሠራዊት ውስጥ ለአገልግሎት ቃል የገባበት ዘመኑን ሲፈጽም ፤ ወይም ሊፈጽም ሦስት ወራት ሲቀረው በአዛዥ መኰንኑ ፈቃድ እንደ ገና ከአንድ ዓመት በላይ በመጨረሻው ከፍተኛ ግምት እስከ ሐያ አንድ ዓመት ፤ ወይም ድንገተኛ ምክንያት የገጠመ እንደ ሆነ እስከ ፳፭ ዓመት ሊቀጠር ይቻላል ።

(፪) በወር ጠባቂ ሰዎች አሥራ አንድ ብር ፤ ሌሎች ተራዎች ዐሥር ብር ። ምክትል ሹማምንቶችም ይህን በመሰለ ከፍ ባለ ግምት የጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንን በሚወስነው ልክ ይቀበላሉ ።

(፫) ማንኛውም ሰው ስለቀለብ በወር በወሩ ስምንት ብር ፤ ወይም በዚሁ ግምት ቀለብ ይቀበላል ።

(፬) ልብስ ፤ የጦር ኤኬኘማና መኖሪያ በነጻ ያገኛሉ ።

፶፫) ማንኛውም የሚጻፍ ፤ ወይም ተመልሶ እንደ ገና የሚቀጠር ወታደር ለመቀጠር ከመጻፉ አስቀድሞ ከዚህ በታች እንደ ተመለከተው ዲክላራሲዮን ማድረግና ይህንም ዲክላራሲዮን ሲያደረግ በፍጹም ሕሊናው ፈቃድ መሆኑን በመሐላ ማረጋገጥ አለበት ።

እኔ በንጉሠ ነገሥቱ ጦር ሠራዊት ውስጥ እንደ አንድ አካል ሆኜ በታማኝነት እንዳገለግልና ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ለወራሾቻቸውና ለተከታዮቻቸው ታማኝና እውነተኛ አገልግሎትን ለመሙላት ለንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዛት ሁሉና ከበላዬ ያሉት የጦር መኰንኖች ለሚያዙኝ ሁሉ እንድታዘዝና ከኔ በላይ ያለው ማንኛውም መኰንን የሚያዘኝን ሥራዎች ሁሉ በእምነት እንድፈጽምና ለንጉሠ ነገሥቱ ጦር ሠራዊት ለወጡት አዋጆች ድንጋጌዎች ፤ ትእዛዞች ፤ ማስታወቂያዎች ፤ ደንቦች ሁሉ የምገዛ በመሆኔ እምላለሁ ።

የሚቀጠረው ሰው ፊርማ ፤ ወይም ምልክት ፤

የምስክሩ ፊርማ ወይም ምልክት ፤

የመኰንኑ ፊርማ ።

፶፬) ማንኛውም ወታደር ያገልግሎት ዘመኑ በጦርነት ጊዜያት በአድማ ፤ ወይም ጠላት በተነሣበት ጊዜያት የሚያልቅ ሲሆን የጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንን እንደሚወስነው መጠን መልቀቁ ቀርቶ ካሥራ ሁለት ወር በማይበልጥ ጊዜ አገልግሎቱን ሳያቋርጥ እንዲቀጥል ይሆናል ።

፶፭) ማንኛውም ወታደር አገልግሎቱ በሚፈጸምበት ጊዜ ቅጣት ካላገኘውና በዚህ አዋጅ እንደተመለከተው

51. In reckoning the service of any soldier for dischange or re-engagement there shall be excluded there-from all periods during which he has been absent from his duty from any of the following causes:—

(a) imprisonment for any cause save that of detention awaiting any trial which results in the acquittal or discharge of the prisoner;

(b) desertion for any period;

(c) absence without leave exceeding forty-eight hours.

52. (1) Any soldier of good character who at any time has completed, or is within three months of completing, the term of his engagement with the colours may, with the approval of his commanding officer, be re-engaged to serve for periods of one year up to a total maximum of twenty-one years, or in exceptional circumstances twenty-five years.

(2) Guardsmen, will receive eleven Maria Theresa dollars a month, other privates ten Maria Theresa dollars, and non-commissioned officers will receive such higher rates as may be decided by the General Officer Commanding the Army.

(3) Every man will receive ration allowance of eight Maria Theresa dollars a month or rations to the same value.

(4) Clothing military equipment and lodging will be provided free.

53. Every soldier who is enlisted, re-enlisted, or re-engaged shall, previous to his being enlisted, re-enlisted or re-engaged, make the following declaration, and shall confirm such declaration by oath in such manner as he may declare to be most binding on his conscience:—

I swear that I shall faithfully serve as a member of the Imperial Army and that I shall be faithful and bear true allegiance to His Imperial Majesty Haile Selassie the First, His heirs and Successors, and will obey all orders of His Imperial Majesty and of the officers placed over me and that I will faithfully perform all tasks which may be imposed upon me by any superior officer set over me, and subject myself to all Proclamations, Laws, Orders, Notices, Regulations, etc., relating to, the Imperial Army.

Signature or mark
of person taking the oath.

Signature or mark
of witness.

Signature of Officer.

54. Any soldier whose period of service expires during a state of war, insurrection, or hostilities, may be detained, and his service prolonged for such further period, not exceeding twelve months, as the General Officer Commanding the Army may direct.

55. Subject to the provisions of Article 51 and the last preceding Article, every soldier who has completed his period

Scanned by CamScanner

ጥፋት አድርጎ የቅጣት ፍርዱ እስኪፈጸም የሚጠባበቅ ካልሆነ ፤ ወይም ተቀጥቶ የቅጣት ፍርዱን እንዲፈጽም ካልሆነ ፤ ወይም የቅጣቱን ጊዜ እንደ ፍርዱ አኳኋን እስኪፈጸም የአገልግሎቱ ዘመን ካልተቀጠለበትና በፍርዱም ከጦር ሠራዊት ወስጥ እንዲወጣ ካልሆነ በተቀር በዚህ አዋጅ በ፶፭ አንቀጽና ከዚህ በላይ ባለው አንቀጽ ላገልግሎት የተቀጠረበት ጊዜ ከተፈጸመ በኋላ አዛዥ መኰንኑ ሊያሰናብተው ይገባል ።

፶፮) ማንኛውም ወታደር ከሥራ መውጣቱን የሚያስረዳ የምስክር ወረቀት እስኪቀበል ድረስ በዚህ አዋጅ ለተመለከቱትና ለማንኛውም ደንቦችና ድንጋጌዎች ሁሉ እየታዘዘ መጠበቅ አለበት ።

፶፯) ማንኛውም ወታደር ተቀጥሮ የወታደርነት ሥራ ሲሠራ የመልቀቂያው ጊዜ ሳይደርስ በማናቸውም ጊዜ ከዚህ በታች በተባሉት ምክንያቶች አዛዥ መኰንኑ ሊያሰጣው ይችላል ።

(ሀ) አገልግሎት ለመቀጠል የአእምሮ ፤ ወይም የአካል ጤና አጥቶ የማይስማማ መሆኑን አንድ የሕክምና ሹም ባስታወቀ ጊዜ ፤

(ለ) በመጥፎ ምግባር ከጦር ሠራዊቱ እንዲወጣ ሲፈረድበት ፤

(ሐ) ለአገልግሎቱ ቃል ኪዳን በሰጠ በሁለት ዓመት ውስጥ አንድ ችሎታ ያለው ወታደር አለመሆኑን አዛዥ መኰንኑ ሲመለከት ፤

(መ) የጦር ሠራዊትን ለመቀነስ ሲያስፈልግ ፤

፶፰) ማንኛውም ወታደር በመኑቀል ሆነ ፤ ወይም የተቀጠረበት ዘመን ተፈጽሞ በመልቀቅ ሆነ ፤ ወይም አገልግሎት ለመቀጠል የማይስማማ (የማይችል) በመሆኑ ወይም ከጦር ሠራዊት በመቀነስ ምክንያት የማስወጫ ምስክር ተሰጥቶት የያዘው ችሎትና ሥልጣን ሁሉ ከላዩ ላይ በመገፈፍ የጦር ሠራዊቱ ክፍል መሆኑ ወዲያውኑ ይቀራል ። አንድ የምስክር ወረቀት ለርሱ ከመስጠቱም በፊት መሣሪያዎችን ፤ ጥይቶችን ፤ ልብሶችን ፤ መለዮ ፤ ሌላውን ዕቃ ሁሉ ለጊዜው የሚያዘው መኰንን ባዘዘው ቦታና ጊዜ ማስረከብ አለበት ።

፶፱) እኛ እንዳስታወቅነው የጦር ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ መኰንን ድንገተኛ ምክንያት በተነሣና ባሳሰበ ጊዜ አስፈላጊ መስሎ እንደታየው ለተወሰነ ዘመን የጦር መኰንኖችና ምክትል ሹማምንት ፤ ወታደሮችም ለመቅጠር ይችላል ። በዚህም ትእዛዝ የተወሰነው ዘመንበየጊዜው እንዲረዝም ፤ እንዲያጥር ፤ እንዲጨመር ፤ እንዲያጐድል ፤ ወይም የአኳኋኑ ዓይነት እንዲበዛ የጦር ሠራዊቱ አዛዥ ከኛ ትእዛዝ ተቀብሎ ለማስታወቅ ይችላል ። ይህም ስለ ሆነ ማንኛውም ሰው ራሱ ካልፈቀደ በተቀር ላገልግሎት በዚህ ክፍል እንዳለው ከተቀጠረበት ጊዜ በላይ እንዲያገለግል አይገደድም ።

or periods of engagement or service according to the provisions of this Proclamation, shall be discharged by his commanding officer, unless at the expiration of any period he is undergoing punishment for or stands charged with, the commission of any offence under this Proclamation, and in case he is undergoing such punishment or is charged with any such offence, his service shall be prolonged and his discharge deferred until such punishment shall have terminated, or until he has undergone his trial and any punishment awarded in respect of the offence with which he is charged, unless his sentence carries with it dismissal from the Army.

56. Every soldier, until he has received a certificate of discharge, shall remain subject to all the provisions of this Proclamation and to all rules and regulations made in pursuance thereof.

57. A soldier may be discharged by his commanding officer at any time during the currency of any term of engagement:—

(a) when pronounced by a medical officer mentally or physically unfit for further service;

(b) when sentenced to be dismissed from the Army for misconduct;

(c) if within two years from the date of attestation his commanding officer shall consider that he is unlikely to become an efficient soldier;

(d) on reduction of establishment.

58. When any soldier ceases to belong to the army, either by being dismissed therefrom, or by being discharged on the termination of his period of engagement, or as unfit for further service, or on reduction of establishment, all powers and authorities vested in him shall, upon a certificate of discharge being given to him immediately cease and determine. He shall before a certificate of discharge is delivered to him, deliver his arms, ammunition, accoutrements, uniform and other appointments which are the property of the Army to such person and at such time and place as shall be directed by the officer under whose command he may be at the time of his ceasing to belong to the Army.

59. It shall be lawful for the General Officer Commanding the Army, subject to Our directions, when occasion arises to enrol for a limited period such number of officers warrant and non-commissioned officers and soldiers as he shall deem necessary; the period or number limited by such order may from time to time be prolonged, shortened, increased, reduced or varied by any subsequent order of the General Officer Commanding the Army.

Provided that any person shall not be compelled to remain in the forces at the expiry of the term of his engagement.

፷ ከዚህ በኋላ ሌላ ሕግ ካልወጣ በተቀር የዚህ አዋጅ ውሳኔዎች ሁሉ ፤ ወይም ይህንኑ ለማሻሻል ፤ ወይም በዚሁ ላይ ለመጨመር የሚወጡት አዋጆች በየጊዜው የሚወጡት ደንቦችና ድንጋጌዎች ሊሠራባቸው እስከሚቻል ድረስ ባለፈው መጨረሻ አንቀጽ እንደተመለከተው የተቀጠሩት መኰንኖችና ምክትል መኰንኖች ፤ ወታደሮችም ሁሉ በጦር ሠራዊት ውስጥ በሚያገለግሉበት ባሉበት ዘመን ሊፈጽሙዋቸውና እነዚህም መኰንኖች ሁሉ በማናቸውም ሐሳብ ለዚሁ የጦር ሠራዊት ሊቀጠሩ ይገባቸዋል ።

፷፩ ይህ አዋጅ በመልካም እንዲፈጸም የጦር ሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ መኰንን ማስታወቂያ ለማውጣት ይችላል ።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፲፱፻፴፮ ዓመተ ምሕረት

ጸ. ት. ወ. ጊዮርጊስ

የጽሕፈት ሚኒስትር ።

60. Save as hereinafter enacted, all the provisions of this Proclamation, and of any proclamation amending or extending the same, and of the rules and regulations which may from time to time be in force, shall, so far as they may be applicable, apply to all officers, warrant and non-commissioned officers and soldiers, enrolled under the last preceding Article, and such officers warrant and non-commissioned officers shall be deemed to be for all purposes part of the army as long as they shall be serving therein.

Done at Addis Ababa this 28th of July, 1944.

TSEHAFE TEZAZ WELDE GUIORGUIS

Minister of the Pen.